# ታጠቅ

ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር
የቋሚ መፅሄት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

---

ሕዝባዊ ጦር ነትና ሕዝባዊ ሠራዊት

---

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፦
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 2 ሐምሌ 1969

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
መጽሔት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethiopian Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አንባቢያችን፣

የሕዝቡን ንቅናቄ ከመሠረቱ ሆኖ ብርብር ለማድከም ያደረገው ሙከራ በላሉ ተባባሪ አርሱን ከንቅናቄያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከቅርብ ጊዜ ጀምሮ፣ ከአስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጎን በመሰለፍ ያለማቋረጥና ያለመታከት ፀረ ኢምፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግል ሲያካሂድ በኖረው ማህበራችንና በነዚሁም አስር ዓመታት ያለተቦጠቡን ነፃነት በመገጠቅ የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግል ሲያስተጋቡ በኖሩት ፓክ የትናየም የተማሪ ማህበራት መጽሔት በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስተማሪያና መቀስቀሻ ሆነው በቆዩት በታጠቅና በትግላችን ስም መጠቀም ጀምረዋል። የዚሁ ፀረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንዲሁም ታጠቅና ትግላችን በአስር ዓመት ቆራጥ ትግል ባተረፉት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖሊሲውን ለመሸፈን ነው። እንዲሁም ከጥንት ሆኖ ያቆዩትን የኢትዮጵያ ተማሪዎችና ተራማጆች አንድነት የማፍረስ ሙከራ ከውጭ ሆኖ ወይ ገበር በመገዛት ለማፋፋም ነው። ይህም እንደሚገባን የተረጋገጠ ነው። ለማገናኘት፣ የተለመደው የመጽሔት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 10364 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዙ፣ የዓለም ዓቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር አባልነትን የሚያመለክቱ ገን የማህበራችን መጽሄቶች ስም የያዙ መጽሄቶች ወዘተ በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር መጽሄቶች አለመሆናቸውን እንድታውቁልንና እንድታስታውቁልን እንጠይቃለን። ለእነዚሁ አይነት መጽሄቶች ተጠያቂው "ዓለም ዓቀፍ ፌዴሬሽን" በሚባል ስም የታወቀው የነ አበራወሰን — መንገሻ ሥዩም የወጣቶች ድርጅት ነው።

ከፋሺስቶችና አወናባጆች ከሪቪዥኒዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በአኢተማ መጽሄት አዘጋጅ ቦርድ

<u>መግቢያ</u>

እነዚህን መስመሮች ስንፅፍ ኢትዮጵያ በአብዮት አፍላ ውስጥ ትገኛለች:: መላው ሕዝብ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ የመደብ ጠላቶቹን በመሣሪያ ትግል ጭምር እየተጋፈጠ ነው:: በመላ ኢትዮጵያ የሕዝባዊ ጦርነት ፅንስ ይታያል:: በዚሁ መጠን ሕዝቡ እየታጠቀ የራሱን ሕዝባዊ ሠራዊት ወደሚገነባበት ደረጃ በፍጥነት በመራመድ ላይ ይገኛል::

ለፀረ ሕዝብ ኃይሎች ይህ ሁኔታ የሚያፀይፍ ብሎም የሚያስፈራ የርስ በርስ ደም መፋሰስ ይሁን እንጂ፣ ለአብዮታውያን የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ወደ ድል የሚቀረብበትና የሚያመራበት ጎዳና ነው:: ስለሆነም አብዮታውያን ይኸን አብዮታዊ ሁኔታ ይደግፉታል:: በተቻላቸውም መጠን ወደፊት እንዲራመድና ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲያመራ ያልተቆጠበ ጥረት ያደርጋሉ::

እኛም በበኩላችን ይህንን ጽሑፍ እንድንጽፍ ያነሳሳን ከዚህ ሌላ ምክንያት የለንም:: ዛሬ በአገራችን የተፀነሰው ሕዝባዊ ጦርነት ወደ ተሟላና መልክ የያዘ ሕዝባዊ የመደብ ጦርነት እንዴት ይሸጋገራል፣ በየቦታው ያቡት የገበሬ ማህበራትና የቀበሌ ማህበራት የፋብሪካ ወዛደሮች ... ወዘተ ጥበቃ ኮሚቴዎች እንዴት ወደ ሕዝባዊ ጦር ይሸጋገራሉ፣ ሕዝባዊ ጦርነት ሕዝባዊ ጦርስ ምን ማለት ነው? እነኚህና እነኚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎች በሚገባ ሊመለሱ ይገባል ብለን ስለምናምን፣ ይህን ጽሑፍ ለመጻፍ አቅደናል::

አንባብያንም ከዚህ ጽሑፍ ብዙ እንደሚማሩ ተስፋ እናደርጋለን:: በበኩላችን አንባብያን በሚሰጡትም አስተያየት ሆነ፣ የማህበራችን አባሎች በዚህ ጽሑፍ ዙሪያ በሚያደርጉት ውይይት ሁላችንም ብዙ ትምህርቶች እንደምንቀስምና በአገራችን የተቀጣጠለው አብዮታዊ ማዕበል ወደ ድል ይጓዝ ዘንድ የምናደርገው አስተዋጽኦ በዚሁ መጠን እንደሚጨምር አንጠራጠርም::

## ሕዝባዊ ጦርነትና ሕዝባዊ ሠራዊት

የማንኛውም አብዮት መሠረታዊ ጥያቄ የስልጣን ጥያቄ ነው:: ማንኛውም
አብዮታዊ ሊያቀርብ የሚገባው ጥያቄ ''እንዴት ስልጣን በሕዝብ እጅ ልትገባ
ትችላለች'' የሚለውን ጥያቄ ነው:: ስለሆነም ሰፊውን ጭቁን ሕዝብ ወደ ስል
ጣን የሚያመራው መንገዱ የትኛው ነው የሚለው ጥያቄ፣ በታሪክ ተደጋግሞ ቀር
ቦዋል ለወደፊትም ይቀርባል:: ብዙውንም ጊዜ በተራማጆች ማሀል ብዙ ክርክር
ያስነሳ ጥያቄ ነው:: በዘባቸ መደቦችም ሆኑ፣ በኮሚኒስት እንቅስቃሴ ውስጥ
ሰርገው የገቡ የቀኝ አድርባዮችና ከላሾች ይህን ጥያቄ አጣመው ለማቅረብ ያል
ተቆጠበ ጥረት አድርገዋል:: ሁሉም፣ ማርክሲዝም ሌኒኒዝም ስለ አብዮታዊ
አመጽ ያስተማረንን ሊያጣምሙና ልዩ ልዩ አድርባይ የቀኝ አስተሳሰቦች ሊያስ
ፋፉ ሞክረዋል፣ ለወደፊትም ይሞክራሉ:: ለዚህ መሠረታዊ ጥያቄ ተገቢ መልስ
መስጠቱ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው የማንኛውም አብዮታዊ ተቀዳሚ ተግባር ነው::

ሕብረተሰብ በመደብ ከተከፈለ ጀምሮ፣ ገዢ መደቦች ለነሱ አገልግሎት
የቆመ የመንግሥት መሣሪያ መስርተው ተገዢ መደቦችን በመበዝበዝ ተገልግለውበ
ታል:: የመንግሥት መሣሪያ ሲባል፣ ገዢ መደቦች የተገዢ መደቦችን አብዮታዊ
እንቅስቃሴ ሊያፍኑበትና ሊደመስሱበት የሚገለገሉበት መሣሪያ ለመሆኑ፣ የዓለም
ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን ያገራችንም ታሪክ ያረጋገጠልን ሃቅ ነው:: ገዢ መደ
ቦች፣ የተገዢ መደቦችን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ለመደምሰስ ያለማቋረጥ በአመጽ
ተጠቅመዋል:: በሌላ በኩል ግን፣ ተገዢ መደቦች ገዢ መደቦችን ለመገልበጥ
በአመጽ እንዳይጠቀሙ፣ ያልገለበጡት ድንጋይ ያላስፋፉት የሰላምና የአብሮ መኖር
አስተሳሰብ የለም::

አንዳንዱ አድርባዮች የገዢ መደቦችን አመጽ እንደሚቃወሙት ሁሉ፣
ተገዢ መደቦች የሚጠቀሙበትን አብዮታዊ አመጽንም ይቃወማሉ:: በሁለቱ ማሀል
ምንም አይነት ልዩነት በለማይታያቸውም አመጽን ከሚገለገልበት መደብ ጋር
አያያዙትም:: ለነዚህ አይነቶቹ ሌኒን ሲመልስላቸው፣ ''ፀረ አብዮታዊ
አመፅንና አብዮታዊ አመጽን የሚለያቸውን ሁኔታዎች ሳይመረምሩ በደፈናው ስለ
አመጽ ማውራት አብዮትን መክዳት ወይም ደግሞ ራስን ደልሎ ሌሎችንም መደለል
ነው'' ይላል::



የሰላም ደቀ መዛሙርት / ፓሲፊስትስ / አመጽ ሲባል፣ መጥፎ
ነገር ይመስላቸዋል:: ስለ ሕብረተሰብ አስተዳደግ ምንም አልገባቸውም ወይም
እንዲገባቸው አይፈልጉም:: አመጽ ሲባል የሚታያቸው አጸያፊ ወገኑ ብቻ ነው::
አመጽ በታሪክ ውስጥ በለሚጫወተው አብዮታዊ ሚና ቅንጣት አልገባቸውም::
ማርክስ ስለ አመጽ ሲጽፍ ''አዲስ ሕብረተሰብን ያረገዘን አሮጌ ሕብረተሰብ
የምታዋልድ ሃኪም'' መሆንዋን የሰላም ደቀ መዛሙርት አያዩትም:: ይህ ማለት፣
የለም ኮሚኒስቶች ወይም ባጭሩ ለአብዮታዊ አመጽ የተሰለፉ ተራማጆች አፍሃሪ
ያች ሊያሳምኑን እንደሚፈልጉት ''ደም የጠማቸው'' ነፍሰ ገዳዮች ናቸው ማለት
አይደለም::

ኮሚኒስቶችም ሆኑ ለአብዮታዊ አመጽ የተሰለፉ ተራማጆች አመጽን
የሚወልደው የሰው በሰው ጭቆና እንደሆነ ያውቃሉ:: ተገዢ
መደቦች ከገዢ መደቦች ብዝበዛ ለመላቀቅ በአመጽ መጠቀም እንዳለባቸው ያም
ናሉ:: ስለሆነም ፀረ አብዮታዊ አመጽን በአብዮታዊ አመጽ ለመደምሰስ ይነ
ሳሉ ማለት ነው::

ማርክስና ኤንገልስ ይህን ጥያቄ በኮሚኒስት ማኒፌስቶ በሚገባ
አስቀምጠዋል:: ''ወዛደሩ አንባገነነቱን የሚመሰርተው ከበርዡውን በአ
መጽ ከደመሰሰ በኋላ ነው'' ይህ ነበር የነማርክስ አስተሳሰብ::
ስለሆነም የአብዮታዊ አመጽ ታሪካዊ ፍቺ ካልገባን፣ የሕብረተሰብ እድገት
ያለአብዮታዊ አመጽ ሊመጣ እንደማይችል ከተረዳን ስለ አብዮት ትክክለኛ
አመለካከት የለንም ማለት ነው:: ''ስልጣን ለሰፊው ሕዝብ እጅ በምን
መንገድ ሊገባ ይችላል'' የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ አንችልም::

ያብዮታዊ አመጽን ታሪካዊ ፍቺ ከተረዳን ግን፣ አንዱ መደብ
ሌላውን ለመበዝበዝ በአመጽ እንደሚጠቀም ሁሉ፣ ተጨቋኙ መደብ ጨቋኙን
መደብ ለመደምሰስ በአብዮታዊ አመጽ መጠቀም እንዳለበት ካመንን፣ በሌላ
አነጋገር ፀረ አብዮታዊ አመጽን በአብዮታዊ አመጽ መደምሰስ አስፈላጊ
መሆኑን ካመንን ''ስልጣን በሰፊው ሕዝብ እጅ የሚገባበትን መንገዱ''
ተልመናል ማለት ነው:: ቢያንስ ለዚህ ጥያቄ ወሳኝ የሆነውን የሕብረተሰብ
ሕግ ተረድተናል::
እንግዲህ የዚህ መሠረታዊ ሕግ ተጨባጭ ትርጉም ምንድነው ለሚለው ጥያቄ
መልስ መስጠት አለብን::

አብዮት ማለት/ የወዛደሩን ስሸሉበት አብዮትም ሆነ በወዛደሩ
የሚመራው ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት/ የገዢ መደቦችን ስርዓት በአብ
ዮታዊ አመጽ መደምሰስ ነው:: የገዢ መደቦችን ስርዓት መደምሰስ ማለት ደ
ግሞ የገዢ መደቦችን የመንግሥት መሣሪያ እንዳለ አስቀምጦ ላይ ላዩን
መጠጋገን ካቢኔውን ወይም ስርዓቱን አስተዳዳሪዎች መቀየር ማለት አይደለም::

ስርዓቱን መደምሰስ ማለት የመንግሥት መሣሪያውን እንዳለ አፍርሶ በሌላ የመንግሥት መሣሪያ መተካት ማለት ነው::

ባንፃሩ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ማለት ሰፊው ሕዝብ ስልጣን ይዞ የገዢ መደቦችን የመንግሥት መሣሪያ ለራሱ ጥቅም የሚያውልበት አብዮት ሳይሆን፣ ሰፊው ሕዝብ በወዛደሩ አመራር ስር የገዢ መደቦችን የመንግሥት መሣሪያ /ፖሊስ፣ ፀጥታ፣ ፍርድ ቤት፣ ወታደራዊ አካል.../ደምስሶ የራሱን አስተዳደር የሚተክበትና የጭቁን ሕዝቦችን አንባገነንነት የሚመሰርትበት አብዮት ነው:: ይህም ደግሞ ያለ አብዮታዊ አመጽ ሊሳካ አይችልም::
በታሪክ በተደጋጋሚ ከሚከሰት እንቅስቃሴ ውስጥ በዚህ ጥያቄ ክርክር ተነስቷል:: በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በነ ካውትስኪ የተወከለው ክላሽ ክንፍም ሆነ የዘመኑ ክላሾች ከካፒታሊዝም ወደ ሶሺያሊዝም በሰላም ወይም በፓርላማ ትግል መተላለፍ እንደሚቻል ሊያሳምኑን ይፈልጋሉ:: ሌኒን ስለዚህ ነጥብ ሲጽፍ እንዲህ ይላል::

•• ካፒታሊስቶች ለብዙሃኑ ጭቁን ፍላጎት በሰላም ይንበረከካሉ ብሎ ማመን፣ በሰላምና በጥገና ወደ ሶሺያሊዝም ማለፍ ይቻላል ብሎ ማመን፣ የንዑስ ከበርቴ ፍፁም ድድብና ምልክት ብቻ ሳይሆን፣ ወዛደሩን ማታለል በካፒታሊዝም ባርነት ተስፋ መጣልና ሃቅን መደበቅ ነው::

በዝባዥ መደቦችን በሙሉ ለማንበርከክ የሚቻለው ከበርቴው በአመጽ ሲገለበጥ፣ ሃብቱ ሲወረስ፣ የከበርቴው የመንግሥት መሣሪያ /ፓርላማ፣ ፍርድ ቤት፣ ወታደራዊ ኃይል፣ ቢሮክራሲ፣ አስተዳደር፣ ማዘጋጃ ቤት....ወዘተ/ ከሥረ መሠረቱ ሲደመሰስና አደገኛ የሆኑት የበዝባዥ መደብ አባሎች ታስረው የካፒታሊዝምን ባርነት እንደገና ለማንሰራራት የማይቀረው ፍላጎታቸው በኃይል ሲገታ ብቻ ነው::•• ሌኒን ሙሉ ስራዎች ቅፅ 31

በታሪክ ውስጥ በተደጋጋሚ የታዩት ክላሽ አዝማሚያዎች ሊያስፋፉት የፈለጉት ሃሳብ፣ ማለትም ካንዱ አይነት ሕብረተሰብ ወደ ሌላ ሕብረተሰብ በሰላማዊ መንገድ መተላለፍ፣ ከሌኒን ጥቅስ አንፃር ሲታይ ያላንዳች መወላወል የጠቀሙ ገዢ መደቦችን ለመሆኑ በቀላሉ መረዳት ይቻላል:: ከማርክሲዝም ሌኒኒዝም አንፃር ዛሬ አብዮታውያን እነዚህን ክላሽ አዝማሚያዎች መታገል አለባቸው:: ብሎም ጭቁን መደቦች ጨቋኝ መደቦችን በአብዮታዊ አመጽ የሚገለብጡበትን መንገድ ከያንዳንዱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አዛምደው መተለም ይኖርባቸዋል::



እንግዲህ የኢትዮጵያን አብዮት በሚመለከተው በኩል የአብዮታዊ አመጽ ታሪካዊ ፋይዳ ይህ ከሆነ ዘንዱ፣ የሕብረተሰብ አስተዳደግም ሕጎችም ከፍ ብለን የዘረዘርናቸው ከሆኑ የኢትዮጵያ አብዮት የተለየ መንገድ የሚከተልበት ምንም ምክንያት ሊኖር አይችልም:: የኢትዮጵያ ሕዝቦች የነፃነት ትግል ድል እንዲቀዳጁ ከፈለግን፣ በወዛደሩ መደብ አመራር የሰፊው ሕዝብ አንባገነንነት የሰፈነበት ሕዝባዊ ስርዓት እንዲመሰረት ከፈለግን ያለ ምንም መወላወል፣ ካሁኑ የፊውዳል ቢሮክራሲያዊው ስርዓት ምሰሶ የሆነው የመንግሥት መሣሪያ የሚደመሰሰበትን መንገድ መተለም ይኖርብናል:: ይህም ሊሆን የሚችለው በአብዮታዊ አመጽ ነውና ከዛሬው ለዚህ ለማይቀረው ፍልሚያ መዘጋጀት አለብን::

ኢትዮጵያ ከፊል ፊውዳል ከፊል ካፒታሊስት አገር እንደመሆንዋ መጠን የኢትዮጵያ አብዮት ፀረ ፊውዳልና ፀረ ኢምፔሪያሊስት አብዮት ነው:: ስለሆነም ብሔራዊ ና ዲሞክራቲክ ይዘት አለው:: በዚህ አብዮት ከሚሳተፉት ጭቁን መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ወዛደሩ የአብዮቱ መሪ ይሁን እንጂ የአብዮቱ ተሸካሚ ሰፊው ገበሬ እንደሆነ ለመገመት አያስቸግርም:: ሰፊውን ገበሬ ያላሳተፈ አብዮት በኢትዮጵያችን ከፍተኛ ውጤት ሊያመጣ ካለመቻሉም በላይ ሊሳካ እንደማይችል የማይታበል ሀቅ ነው:: ይህም በመሆኑ ኢትዮጵያን በመሰለች አገር የሚካሄደው አብዮት የገጠር አብዮት እንጂ ሌላ ሊሆን አይችልም::

ስለዚህም ኢትዮጵያን ለብዙ ዓመታት የገዟትን ፋውደ ከበርቴ ስርዓት ለመደምሰስ ሰፊው ሕዝብ በአብዮታዊ አመጽ ነቅቶ ተደራጅቶና ታጥቆ አብዮታዊ ትግሉን ሲያንቀሳቅስ በግዱ ከገጠር ተነስቶ ገጠሩን ነፃ አውጥቶ ከተማውን የሚከበበትና ብሎም በቁጥጥሩ ስር የሚያውልበት አረማመድ መከተል ይኖርበታል:: ይህም ረጅምና መራራ ሕዝባዊ ጦርነትን ይጠይቃል::

ማኦ ትሴ ቱንግ ስለ ሕዝባዊ ጦርነት ረጅምና መራራነት ሲያትቱ የሚቀጥለውን ጽፈው ነበር::

•• ጠላታችን ኃይለኛ ነው:: ነገር ግን ለሱ አመቺ ያልሆኑ ሁኔታዎች ኃይሉን እየበረበሩት ነው:: እስካሁን ግን የበላይነቱን ጥያቄ ውስጥ አላስገቡትም:: እኛ ደካሞች ነን ነገር ግን ለኛ አመቺ የሆኑ ሁኔታዎች ድካማችንን አላስቀረልንም:: ስለሆነም ጠላታችን ለጊዜው ኃይለኛ ቢሆን እኛ ለጊዜው ደካሞች ነን::.....እንግዲህ በዚህ የትግል ምዕራፍ የኛ መሸነፍና የጠላታችን ማሸነፍ ፍፁም ውሸት ይሆናል ማለት ነው:: የምናካሄደውም ጦርነት ረጅም የሚሆነውም ለዚሁ ነው::

.....በጦርነቱ ልዩ ልዩ ደረጃዎች፣ ትክክለኛ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ታክቲክ በተከተልን መሠረታዊ ስህተቶች ካለፈጸምንና በተቻለን መጠን ኃይላችንን በሙሉ ከተጠቀምንበት እና አመቺ የሆኑትና ለጠላታችን የማይመቹት ሁኔታዎች እየጠነከረ ይመጣሉ::

ይህም፣ ጠላት ኃይለኛ፡እና ደካማ፣ጠላት አሸናፊ እና ተሸናፊ የነበረንበትን የመነሻ ሁኔታ ይቀይረውና በሌላ የትግል ደረጃ ሁኔታው በመሠረቱ ይቀየራል:: የዚህም ለውጥ ውጤቱ የጃፓን መሸነፍና የቻይና ማሸነፍ ይሆናል::"

የኢትዮጵያ ሕዝቦችም አሁን ካሉበት ሁኔታ ወደ አሸናፊነት ለመድረስ ገና ረጅምና መራራ ትግል ይጠብቃቸዋል:: በተወሰነ የትግል ደረጃም ዛሬ የተፀነሰው የጦር ትግል ወደ ረጅምና መራራ የጦር ትግል ማምራቱ አይቀርም:: አብዮታውያንም ይህንን ሃቅ ተረድተው ከሁኑ ሊዘጋጁለት ይገባል::

በሚቀጥሉት ክፍሎች የሕዝባዊ ጦርነትንና የሕዝባዊ ሠራዊትን ምንነት ለማሳየት እንሞክራለን::



1. ህዝባዊ ጦርነትን ልዩ ነቱን የሚያደርጉት ነጥቦች::

ሀ/ ህዝባዊ ጦርነት ጭቁንና ተፅዕኖን የሚታገል፣ የውጭ ሃይሎችንና በዝባዥ መደቦችን በሰፊው ህዝብ ላይ የሚያወርዱትን ፀረ አብዮት አመጽ የሚቋቋምና ለእኩልነት፣ለሰላምና ለዲሞክራሲ የሚታገል፣ ያንድን አገር ብሄራዊ ነፃነት ለማስከበርና ሰፊውን ህዝብ ከብዝበዛ ነፃ ለማውጣት የሚደረግ ጦርነት ነው::ስለዚህም ህዝባዊ ጦርነት በሰፊው ህዝብ ሙሉ ተሳታፊነት የሚካሄድ ጦርነት ይሆናል::

የበዝባዥ መደብ የጦር ሰልቶች በበቂ ከታጠቁ፣ዘመናዊ መሣሪያ ካላቸውና በጦር ስልት የሰለጠኑ ወታደሮች ካሰለፉ ማንኛውንም ህዝባዊ አብዮታዊ አመፅ ሊደመስሱ የሚችሉ ይመስላቸዋል::በዚህውንም ጊዜ በዝባዥ መደቦች የሚጋፈጧቸው አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች በመሣሪያ ደረጃ ደካማ ከመሆናቸውም በላይ በጦርነት ስልት በኩል በቂ ልምድና ትምህርት የሌላቸው በመሆናቸው፣ እነዚህን አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች መደምሰስ ፍጹም ቀላል ይመስላቸዋል::ሆኖም ግን በታሪክ ተደጋግሞ እንደታየው ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ነቅተው፣ተደራጅተው፣በመጠኑም ቢሆን ታጥቀው የተነሱ ህዝቦች ከፍተኛ ወታደራዊ ሃይል ያላቸውን መንግሥታትም ሆነ ሠራዊቶች ድል መተዋል::የቬትናምን ምሳሌ ብንወስድ፣በ1946 የፈረንሳይ ኮሎኒያሊስቶች የቬትናም ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክን እንደገና በቁጥጥራቸው ስር ለማዋል ሲነሳሱ፣ባጭር ጊዜ ውስጥ የቬትናምን ህዝብ አመጽ ለመደምሰስ የሚችሉ መስሏቸው ነበር::የፈረንሳይ ጦር ሃላፊ የነበረው ጄኔራል ለክሌርክ ቬየትናምን በአስር ሳምንት ውስጥ በቁጥጥሩ ስር ለማዋል እንደሚችልና የገጠመውን ህዝባዊ ረዚስታንስ /"ረዚስታንስ" / ለመደምሰስ የሚያስፈልገውን ዘመቻ እንደወታደራዊ ሽርሽር እንደሚቆጥረው ተናግሮ ነበር::የፈረንሳይ ጦር መሪዎች ይህንን ለማለት የበቁት የቬትናም ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ሠራዊት በቁጥርም ሆነ በጦር መሣሪያ ደካማ ከመሆኑም በላይ ገና በቅርብ የተቋቋመና በጦር ስልት ልምድ በሌላቸው መኮንኖች የሚመራ ሠራዊት በመሆኑ ነው::እርግጥ በዚን ጊዜ፣የፈረንሳይን ሁለተኛ ክፍለ ጦርና የቬትናምን ሠራዊት ስናወዳድር የቬትናም ሠራዊት በጣም ደካማ ነበር::የቬትናም ሠራዊት አይሮፕላንና ታንክ ይቅርና በቂ የጥይት ክምችት እንኳ የለውም ነበር::ስለሆነም በፈረንሳይ ጦር ሠራዊት ዘንድ፣የቬትናም ወታደሮች ጥይታቸውን ጨርሰው ያላቸው እድል እጅ መስጠት ብቻ ነው የሚል ግምት ነበር::

ይሁንና፣ፈረንሳዮች ያልተረዱት አንድ ሃቅ ነበር::ይህም የቬትናም ሠራዊት ህዝባዊ ሠራዊት እንደነበረና የቬትናም ህዝብ የፈረንሳይን ወረራ ለመቋቋም የቀሰቀሰው ጦርነት ህዝባዊ ጦርነት እንደነበረ ነው::በፈረንሳይ ኮሎኒያሊስቶችና በቬትናም ማህል የተካሄደው ጦርነት ሁለት ሠራዊቶችን ፊት ለፊት

ያጋጠመ ጦርነት ብቻ አልነበረም:: የፈረንሳይ ኮሎኒያሊስቶች ቪየትናምን ሲወሩ የመላ ቪየትናምን ህዝብ ቁጣ እንደቀሰቀሱ አልተረዱም:: የመላ ቪየትናም ህዝብንም ቁጣ ስለቀሰቀሱ የመላ ቪየትናም ህዝብ ባንድነት ተነሳባቸው::ስለ ስር ሳምንት እንደመሰሰዋለን ያሉት ህዝባዊ አብዮታዊ አመፅ ጊዜ ፈጀ እንጂ ውርደትን ሊያከናንባቸው ቻለ::በቀላሉ የተመለከቱት ወረራ ባይሳካላቸው ሲቀር ጊዛቸውን ከቪየትናም ጠቅለለው እንዲወጡ ተገደዱ::

የቡርዥዋ የጦር ስልተኞች እስከዛሬ ስለቪየትናም ድል መምታት ይደነቃሉ:: የቪየትናም ሠራዊት እንዴት ፈረንሳይን የመሰለች፣ለዚያውም በአሜሪካን የተደገፈች ተለቅ ኢምፔሪያሊስት አገርን ሊያሸንፍ ቻለ ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ፣ይህ ሊሆን የቻለው የቪየትናም ወታደሮች ቁራጥና ዘዴኞች ስለሆኑ ነው ይላሉ:: የቪየትናም ወታደሮች ቁራጥነት ለቪየትናም ህዝብ አሸናፊነት በርግጥ የተወሰነ ሚና ተጫውቷል:: ነገር ግን የቪየትናም ህዝብ ድል ሊቀዳጅ የቻለው ቁራጥ ስለሆነ ብቻ ሳይሆን <u>በመሰረቱ</u> ያካሄደው ጦርነት ለህዝብና በህዝብ የተካሄደ ጦርነት በመሆኑ ነው::

ጄኔራል ቮን ጊያፕ ስለዚሁ ሲያትት እንዲህ ይላል:—

> "የቪየትናም ህዝብ ሊያሸንፍ የቻለው ያካሄደው የነፃነት ጦርነት ህዝባዊ ጦርነት ስለነበር ነው::...ህዝባዊም ሊሆን የቻለው፣የጦርነታችን የፖለቲካ ዓላማ ኢምፔሪያሊዝምን ደምስሶ ብሄራዊ ነፃነታችንን ማስጠበቅና ባለባታዊ ስርዓትን ገርስሶ መሬትን ላራሹ ማደል ስለነበር ነው::በሌላ አነጋገር የቪየትናምን ህብረተሰብ ሁለት መሠረታዊ ቅራኔዎች መፍታት —ባንድ በኩል በአገሪቱና በኢምፔሪያሊስቶቹ ማሀል የነበረው ቅራኔ በሌላ በኩል በሰፊው ሕዝብ በተለይም በገበሬና በባለባት ማሀል የነበረው ቅራኔ— ብሎ የቪየትናም አብዮት ወደ ሶሻሊዝም የሚያመራበትን ጉዳና መክፈት ነበረብን..."

የቪየትናም ምሳሌ የሚያሳየን፣አንድ ህዝብ ለነፃነት ለሰላምና ለዲሞክራሲ ለመታገል ቆርጦ ከተነሳ፣በዚህም አቋሙ ትክክለኛ አመራር ካለው ማንኛውንም የበዝባዥ ሃይል ለመደምሰስ እንደሚችል ነው::

ትክክለኛ አመራር ካለው ማለትም፣ህዝባዊ ጦርነት ለህዝብ በህዝብ ከመሆኑም በላይ ይህን ጦርነት የሚመራ ትክክለኛ የፖለቲካ መሥመር ያለው አካል ያስፈልገዋል ማለት ነው::ከፍ ብለን የጠቀስነው የቪየትናም ምሳሌም ቢሆን፣እንደሚያስተምረን፣ህዝባዊ ጦርነት አሸናፊ ሊሆን የቻለው በማርክሲዝም



ሌኒኒዝም የታነፀ የወዛደር ፖርቲ ስለነበረው ነው:: ይህን የመሰለ አመራር ከሌለው ማንኛውም ሕዝባዊ ጦርነት የፖለቲካ ዓላማውን በትክክል ከግቡ ሊያደርስ ስለማይችል በሕዝብ ለሕዝብነቱ የተሟላ ሊሆን አይችልም::

ጄኔራል ቮን ጊያፕ ስለዚሁ ሲያትት እንዲህ ይላል:—

> "የሕዝቡን መሠረታዊ ፍላጐቶች በሙሉ ያዘለ ዓላማ ብቻ ይዞ መቅረብ ብቻ አይበቃም ነበር:: ሰፊውን ሕዝብ ለማንቃት ለማስተማርና ለማስረታታት፣ ለብሔራዊ ክብራቸን በምና ደርገው ትግል ለማደራጀት አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ያስፈልግ ነበር:: በዚህ ተግባር መላ ብሔራዊ ኃይሎችን ለመሰብሰብና ለተባበረው ብሔራዊ ግንባር ስፊ መሠረት ለመስጠት ፖርቲው በሙሉ ልብ ተሰማራ::"

የፖርቲው አመራር፣ የሚያስፈልገው፣ በየትግሉ ወቅት ትክክለኛ የፖለቲካ አመራር ለመስጠት ብቻ ሳይሆን፣ የወዛደረ ፖርቲ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ከሚታገሉ ኃይሎች አንደኛውና ግንባር ቀደሙ እንደመሆኑ መጠን ሰፊውን ሕዝብ በትግሉ ለማሰለፍም ጭምር ነው:: በማርክሲዝም ሌኒኒዝም በታነፀ የወዛደር ፖርቲ የሚመራ ሰፊውን ሕዝብ ያሰለፈ ሕዝባዊ ጦርነት አሸናፊነቱም የተረጋገጠ ነው:: ይህንን ሃቅ የዓለም ሕዝቦች አብዮታዊ ታሪክ በሚገባ አስመስክሯል::

ለ/<u>ሕዝባዊ ጦርነትን ዓይነተኛ የሚያደርገው ሁለተኛ ነጥብ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የሚደረግ ጦርነት ከመሆኑም በላይ፣ ለሶሺያሊስት አብዮትና ለብሔራዊ ነፃነት እንቅስቃሴዎች ዓለም ዓቀፍ ሁኔታ ዓመቺ በሆነበት ዘመን የሚካሄድና፣ ሕዝቦች ኢምፔሪያሊዝምን ከምድር ገፅ ለማጥፋት ከለጥናፍ እስከ አጥናፍ በተነሱበት ዘመን የሚካሄድ ጦርነት መሆኑ ነው::</u>

አሁን ያለንበት ዘመን የዓለም ዓቀፍ ሁኔታ ለሕዝባዊ ጦርነቶች አመቺ የሆነበት ዘመን ነው:: የኦክቶበር/ የጥቅምት / 1917 የሰብየት ሕብረት አብዮት በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ከፍቷል:: ይህ ምዕራፍ ኢምፔሪያሊዝም የሚደመሰስበትን በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ሶሺያሊዝም የሚያብብበት ምዕራፍ ነው::

አሁን ባለንበት ዘመን በማንኛውም ቦታ የሚደረጉ አብዮቶች የዓለም ዓቀፍ አብዮቶች አካል ናቸው::

በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀጣጠሉት የሶሽያሊስት አብዮቶችም ሆኑ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮቶች የታሪክን አረማመድ የተከተሉ ናቸውና ዐርስ በርሳቸው ከመደጋገፋቸውም በላይ፣ የጋራ ጠላታቸውን ባንድነት እየመቱ ወደፊት ይራመዳሉ:: ለነፃነትና ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ሕዝቦች በየጊዜው የዓለም የሶሻሊስትና ሕዝባዊ መንግሥታት ዓለም ዓቀፋዊ ድጋፍ አይለያቸውም:: በሶ ያለም ሕዝቦች፣ የቡዝቧዥ ኢምፔሪያሊስት አገር ሕዝቦችም ጭምር ለነዚሁ ትግሎች ድጋፋቸውን አይቀጥቡም::

ኢምፔሪያሊስቶች ግን በታሪክ የተተፋን ሥርዓት ስለሚወክሉ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተዳከሙ፣ የራሳቸው ሀገር ሕዝቦች እየተነሱባቸው ወደ አዘቅት በመግባት ላይ ይገኛሉ::

ስለዚህም የዓለም ሕዝቦች አብዮት በማያቋርጥ ሁኔታ በአጥቂነት ወደፊት ሲራመዱ፣ ኢምፔሪያሊስቶች ግን በተከላካይነት በዝበዛቸውን ለመቀጠል ሲጣጣሩ ይታያሉ::

በዚህ ታሪካዊ ሁኔታ የዓለም ሕዝቦች ለነፃነት ለዲሞክራሲና ለሶሺያሊዝም የሚያደርጉት ትግል ወደ ድል ይራመዳል:: እያንዳንዳቸው በዓለም ዓቀፍ የአብዮት ኃይሎች የተደገፉ ከመሆናቸውም በላይ ከሁሉ አስቀድመው በሕዝባቸው ላይ ስለሚተማመኑ የትግላቸው የመጨረሻ ውጤት አሸናፊነት እንጂ ተሸናፊነት አይደለም::

በአጠቃላይ ሲታይ አሁን ባለንበት የአብዮት ዘመን ሕዝባዊ ጦርነት አይነተኛ የሚያረጉት ሁለት ነጥቦች እነዚሁ ናቸው:: ከዚህም ትንተና ለመረዳት የቻልነው፣ ሕዝባዊ አብዮቶች በሕዝባዊ ጦርነት ነፃነታቸውን ለመቀዳጀት የሚያደርጉት ትግል ድል እንደሚመታና ጠላቶችን እንደሚደመስስ ነው::

ይህ ቢሆን ግን አንዱ ሕዝባዊ ጦርነት ሊከተለው የሚገባው ፖለቲካ ስትራቴጂና ታክቲክ እንዳለ፣ ይህም ደግሞ በሰፊው ሊጠና እንደሚገባው የማይታበል ሃቅ ነው:: አብዮታውያንም ከዓለም ሕዝቦች ትግል ትምህርት በመቅሰም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም በለጠር ትግል ያስተማረንን በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አዛምደን፣ ለነፃነት ትግላችን የሚጠቀብንን የማይቀረውን ሕዝባዊ ጦርነት በተከከለ እንመራ ዘንድ፣ ስለ ሕዝባዊ ጦር ፖለቲካል ስትራቴጂካልና ታክቲካል ይዘቶች በቂ እውቀት ሊኖረን ይገባል::

በሚቀጥሉት ገጾች ይህንን ይዘት ለመመርመር እንሞክራለን::



## 2. በሕዝባዊ ጦርነት ውስጥ የፖለቲካና ወታደራዊ ድርጅቶች

ሌኒን ስለ ሕዝባዊ ጦርነት ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር::

> ‘‘ጦርነት ለማካሄድ የሕዝቡ ኃይሎች በሙሉ መሰብሰብ አለባቸው:: መላ አገሩ ወደ አብዮት ካምፕ እንዲሆን ያስፈልጋል::....... የሃገሪቱ ሀብትና የሃገሪቱ ኃይሎች በሙሉ ለአብዮቱ ጥበቃ መዋል አለባቸው::’’

አንድን ሕዝብ ወደ ሕዝባዊ ጦርነት ለማሰማራት ልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲኖሩ ያስፈልጋል:: እነዚሁ የፖለቲካ ድርጅቶች ያስገሪቷን ጭቁን መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ለጦርነቱ የሚያሰለፉ ድርጅቶች ናቸው:: እነዚሁ ድርጅቶችም ለሕዝባዊ ሠራዊቱ መፈጠርና መጠናከር መሠረት ይሆናሉ::

በሌላ አነጋገር ሰፊው ሕዝብ በሚሰማራበት ብሔራዊና ዲሞክራቲክ ትግል የሚመሩት ድርጅቶች መቋቋም ይኖርባቸዋል ማለት ነው:: እነዚሁም የሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር አካል የሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶችና ፓርቲያቸ በተለይም የግንባሩ መሪ የወዛደሩ ፓርቲ ናቸው:: የነዚሁ ድርጅቶች መጠናከርና በወዛደሩ ፓርቲ አመራር ስር ባንድነት መሰብሰብ ሰፊውን ሕዝብ ወደአብዮታዊ ትግል ለማሰለፍ ከመርዳትም በላይ፣ ከሰፊው ሕዝብ ማህል ለሚፈልቀው ሕዝባዊ ሠራዊት ምንጭ የሚሆኑት እነዚሁ ድርጅቶች ናቸው:: መላው ሕዝብ ከገጠር እስከ ከተማ ከፋብሪካ እስከ ልዩ ልዩ አስተዳደሮች ድረስ በፖለቲካ ድርጅቶች በወዛደሩ ፓርቲ መጠናከርና የልዩ ልዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች በዚሁ ፓርቲ አመራር ስር ማሰብ ሕዝባዊ ሠራዊት ለማቋቋም ከሚደረገው ትግል ተለይቶ ሊታይ አይችልም:: ለአብዮታዊ ትግሉ በፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥጥር ስር ያለው ሕዝባዊ ሠራዊቱ ፈለፈት በጦር ኃይል እንደሚጋለጥ ሁሉ የተባሉት የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ መለሰው ከሕዝባዊ ሠራዊቱ ጋር ትግላቸውን በማቀነባበርና በልዩ ልዩ መልክ በትግሉ በመሳተፍ ሕዝባዊ ሠራዊቱን ይረዱታል::

ኢትዮጵያን በመሳሰሉ አገሮች ማለትም ሕዝቡ በብዛት በገበሬ ክፍል ውስጥ የሚጠቃለልበትና የወዛደሩ ቁጥር አነስተኛ በሆነበት በታ፣ የሕዝባዊ ግንባሩም ሆነ የሕዝባዊ ሠራዊቱ አባሎች በብዛት ገበሬዎችና በጥቂቱ ወዛደሮች እንደሚሆኑ ለመገመት አያስቸግርም:: ስለሆነም በተለይ በንደዚህ ዓይነቱ ሀገር ከፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ በተለይ የወዛደሩን ፓርቲ ለማጠናከርና የወዛደሩም ፓርቲ በሕዝባዊ ሠራዊት ላይ የሚያደርገው ቁጥጥር እንዲጠነክር ባይ ታክቶ መስራት ያስፈልጋል:: ይህም ማለት በንቃትና በድርጅት የበሰሉ የፖለቲካ ድርጅቶች እንደሚያስፈልጉ ሁሉ በሠራዊቱም ዘንድ ለንቃትና ለፖለቲካል ብስለት የሚደረገው ትግል የሚያሰፈው የፖለቲካ ድርጅቶቹ ሕዝባዊ ሠራዊቱን በጥብቅ ለማስተባበር በሚደረገው ትግል ነው::

## 3. ሕዝባዊ ሠራዊቱ በመሠረቱ ሶስት አካሎች ይኖሩታል፡፡

ሕዝባዊ አብዮታዊ አመጽ የአብዮት ከፍተኛው ደረጃ እንደመሆኑ መጠን ማንኛውም አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሰፊውን ሕዝብ በወዛደሩ መደብ አመራር ስር የሚሰበስብ ሕዝባዊ ግንባርና የግንባሩ መሪ የወዛደሩ ፓርቲ እንደሚያስፈልገው ሁሉ፣ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊትም እንደሚያስፈልገው የማይታበል ሃቅ ነው፡፡

ይህ ሕዝባዊ አብዮታዊ ሠራዊት የሚፈልቀው ከፖለቲካ ድርጅቶች ስለሆነም ሕዝባዊ ሠራዊት አብዮቱ ባደገ ቁጥርና የፖለቲካ ድርጅቶቹ በተጠናከሩ ቁጥር የተለያዩ የእድገት ደረጃ ይከተላል፡፡ ለምሳሌ አሁን የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ትግል የደረሰበትን ደረጃ ብንመለከት ኪሆኑ የሕዝባዊ ሠራዊት ፅንሶች ይታያሉ፡፡ እነሱም የገበሬ ማህበራት የቀበሌ ማህበራት የፋብሪካ ወዛደሮች.....ወዘተ የጥበቃ ጓዶች ናቸው፡፡ እንግዲህ አብዮቱ ግቡን እንጎታ ከተፈለገ እነዚህ የሕዝባዊ ሠራዊት ፅንሶች ወደ ጠንካራ ሕዝባዊ ሠራዊት ወታደራዊ ኃይል የሚቀየሩበት ሁኔታ መፈጠር አለበት ማለት ነው፡፡ብሎም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የተሟላ ሠራዊት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል፡፡ ይህ ሠራዊት ሶስት ዋና ዋና አካሎች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ አካሎች በተለያዩ የትግል ደረጃዎች ለየ ለየ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ሆኖም ግን እያንዳንዳቸው አይነተኛ የሚያሬግ ይዘት አላቸው፡፡

### አንደኛ — ሕዝባዊ ሚሊሺያዎች የጥበቃ ጓዶችና የገሪላ ኃይሎች፡፡

እነዚህ አካሎች የሰርቶ አደሩ ሕዝብ መሠረታዊና ቀጥተኛ የመከላከያ ኃይሎች ናቸው፡፡ ከሰፊው ሕዝብ የለት ተለት ኑሮ ይበቅላሉ፡፡ በርባታ ይሰማራሉ፡፡ ሕዝባዊ ስልጣን በየገጠሩ በየከተማው በየፋብሪካው በየቀበሌው....ወዘተ የሚመረኮዘው በነዚህ ኃይሎች ላይ ነው፡፡ በተቻለ መጠን ሁኔታው በሚፈቅደው መንገድ በሃገሪቱ በሙሉ እንዲስፋፉ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተገኘው መሣሪያ፣ ዘመናዊም ሆነ አልሆነ፣ በመጠቀም በየቦታው የፀረ አብዮትን ኃይሎች የሚጋፈጡትና የሚያዳክሙት እነዚህ ኃይሎች ናቸው፡፡ ለሕዝባዊ ሠራዊቱ ዋና ዋና አካሎች ታጋዮች የሚመለምሉ የሚያበረክቱ እነሱው ናቸው፡፡



### ሁለተኛ— ያካባቢ ሠራዊቶች / “ሪጅናል ትሩፕስ”

በአንድ አካባቢ ለማካሄደው የጦር ትግል የደም ስሮች ናቸው፡፡ ከካባቢው ሁኔታ ጋር በተዛመደ ሁኔታ ይቋቋማሉ፡፡ ካስፈለገ ብቻቸውን አለበለዚያም ከሕዝባዊ ሚሊሺያዎች፣የጥበቃ ጓዶችና የገሪላ ተዋጊዎች ወይም ደግሞ ከዋና ሠራዊቱ ጋር በመተባበር በካባቢው ያለውን የጦር ትግል ለማካሄድ መቻል አለባቸው፡፡ በካባቢው የጠላትን ሰፈር መደምሰስ፣ በካባቢው ገሪላን ማስፋፋት ሕዝቡን መጠበቅና፣ የሕዝባዊ ሥልጣን መሠረቶችን ማጠናከር አይነተኛ ተግባራቸው ነው፡፡

### ሶስተኛ — መደበኛ ሠራዊት / “ሬጉላር ትሩፕስ”

መደበኛ ሠራዊቱ ተነቃናቂና በአገሪቱ በሙሉ በተለይም በስትራቴጂካል ቦታዎች የሚዋጋ ጠንካራ ሠራዊት ነው፡፡ ቢቻል ለየ ለየ ጦሮች ይኖሩታል፣ /ጠንካራ የምድር ጦር ቢቻል አየር ኃይልና የባህር ኃይል/፡፡ ጠላትን በከፍተኛ ደረጃ በተሳለቀ ውጊያዎች ለመቋቋም ብቁ መሆን አለበት፡፡ ይህ ሠራዊት አንዱ ውጊያ ውስጥ በሚሰማራበት ጊዜ ድሉን እንደሚቀዳጅ እርግጠኛ መሆን አለበት፡፡ ብሎም በጦር ሜዳ ያለውን የኃይል አሰላለፍ እየቀየረና ጠላትን እየደመሰሰ የሚራመደው ይህ ሠራዊት ይሆናል፡፡

የሕዝባዊ ሠራዊት ሚና ጠላትን መደምሰስ ብቻ ባይሆን ሕዝቡን መጠበቅ፣ በየቦታው የፖለቲካ ድርጅቶችንና ሕዝባዊ ስልጣንን ማጠናከርና በምርት መሳተፍም ጭምር ነው ማለት ነው፡፡

በጦር መሳሪያ በኩል ዋናና መሠረታዊ ድጋፍ ሰፊው ሕዝብ ነው፡፡ ቢቻል የጦር መሣሪያ ራሱ ሕዝቡ እንዲሰራና በተለይ ከጠላት በሚነጠቀው መሣሪያ መገልገል፣ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከወዳጅ አገሮች ርዳታ መጠየቅ፣ የጦር መሣሪያ ምንጮች ይሆናሉ፡፡
ከፍ ብለን በሶስት የከፈልናቸው የሕዝባዊ ሠራዊት አካሎች የሚቋቋሙት የጦር ትግሉ እያደገ በሄደ ቁጥር ነው፡፡ በያንዳንዱ የትግል ደረጃ በሶስቱም አካሎች እያደጉ በለሚሄዱ በማህላቸው ሊኖር የሚገባው መቀነባበር በዚሁ መጠን እየተጠናከረ ይሄዳል፡፡

በማንኛውም ሁኔታ ግን ሕዝባዊ ሠራዊቱ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በጥብቅ መተባበር አለበት፡፡ የሕዝባዊ ሠራዊቱ ማንኛውም አካል አመራርም በማንኛውም ጊዜ በወዛደሩ ፓርቲ አመራር ስር መዋል አለበት፡፡

በፖለቲካ ድርጅቶችና በሕዝባዊ ሠራዊቱ ማሀል ስላለው ግንኙነት ሕዝባዊ አብዮታዊ እንቅስቃሴው እያደገ ሲሄድ፣ብሎም ሰፊው ሕዝብ የሚያካሂደው የጦር ትግል እየተጠናከረ ሲመጣ የሚቀጥሉት ነጥቦች መሟላት ይኖርባቸዋል::

— ዋናውና መሠረታዊው መርሆ፣ በሕዝባዊ ሠራዊቱ ላይ በየደረጃውና በማያወላውል ሁኔታ የወዛደሩ ፓርቲ የሚኖረው ቁጥጥር እየተጠናከረ መሄድ አለበት::

— የሕዝባዊ ሠራዊቱ ዋና ኃይል የሆነውን የፖለቲካ ቅስቀሳ በማያቋርጥ ሁኔታ በሠራዊቱ መጠለ ማካሄድ::

— የሠራዊቱ ካድሬዎችና ታጋዮች የፓርቲውን መስመርና የትግሉን የፖለቲካ ዓላማዎች እንዲረዱ፣ የፓርቲውን መስመርና ወታደራዊ ተግባራቸውን እንዲያገናዝቡ ማድረግ፣ብሎም ማርክሲዝም ሌኒኒዝም እንዲያዋሃዱቸው፣ የመደብ ንቃታቸው ከብሄራዊ ስሜታቸው ጋር እንዲጣጣምር፣ ለአገራቸውና ለሶሻሊዝም ያላቸው ፍቅር እንዲጣብርና ጠላትን ለመደምሰስ ያላቸው ቆራጥነት በየጊዜው እየተጠናከረ እንዲሄድ ማበረታታት ያስፈልጋል::

— የፓርቲውን ድርጅቶች ማጠናከር::

— ለፓርቲው አብዮታዊ ትግል በሙሉ ልብ የተሰለፉ ካድሬዎች መመልመልና ሠራዊቱን ለማደራጀትና ለመምራት ማሰማራት::

— ሳንትራሊዝም ዲሞክራቲክን ማጠናከርና ፓርቲውም ሆነ ሠራዊቱ ክበረት በጠነከረ ዲሲፕሊን እንዲሰሩ ማድረግ:: በሠራዊቱ ማሀል የአንድነት ስሜት እንዲሰፍን በሠራዊቱና በሕዝቡ ማሀል የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር መጣር::

## 4. የሕዝባዊ ጦርነት የእድገት ደረጃዎችና አረማመድ

አንድን አገር ከመደብ ጠላቶችም ሆነ ከውጭ ኃይሎች ነፃ ለማውጣት ሰፊው ሕዝብ በአብዮታዊ አመጽ መጠቀም እንዳለበት አይተናል:: ይሁንና ከተባለው ግብ ለመድረስ በልዩ ልዩ የትግል ደረጃዎች ማለፍን ይጠይቃል:: ራሱ ሕዝብን በፖለቲካ ድርጅቶች ማደራጀት ብሎም ቀስ በቀስ ሕዝባዊ ሠራዊት ማቋቋም ጊዜን የሚጠይቅና መራራ ትግልን የሚጠይቅ ተግባር ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ በፀረ ሕዝብ መደቦችና በኢምፔሪያሊዝም ተፅኖ ስር ያለን አገር ነፃ ማውጣት ረጅምና መራራ ትግልን የሚጠይቅ ተግባር ነው::



አንድን አገር ነፃ ለማውጣት በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ጠንካራ መሰረት የጣሉ ድርጅቶች ከሌሉ ከነዚህ ድርጅቶች ጋር በጥብቅ የተያያዘ ሕዝባዊ ሰራዊት ከሌለ፣ ከሕዝቡ የንቃትና የትግል ደረጃ አብሮ የሚራመድ የትግል ስልት ከሌለ፣ ወደፊት መራመድ አይቻልም:: የዚህን አረማመድ ልዩ ልዩ ደረጃዎች ለማየት እንሞክር::

ሀ/ ከሁሉ አስቀድሞ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ሰፊ የፖለቲካ መሠረት መጣል ያስፈልጋል:: ብሎም ቀስ በቀስ ይህንን የፖለቲካ መሠረት ወደ ጠንካራ የደጀን ሠፈር መቀየር ያስፈልጋል::

ማንኛውም ሕዝባዊ ጦርነት ሲጀምር በወዛደሩ ፓርቲ በሚመራው ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባር ሙሉ ቁጥጥር ስር የዋለና ከጠላት ነፃ የወጣ ሰፈር የለውም:: በዚህ ጊዜ ለአብዮታዊ እንቅስቃሴው ድጋፍ የሚሆኑት የሰፊው ሕዝብ አብዮታዊ ድርጅቶች የሰፊው ሕዝብ አገር ወዳድነትና ለአብዮት ያለው ድጋፍ ነው:: ስለዚህም በንዲህ ዓይነቱ ሁኔታ ''ሰፊው ሕዝብ ባለበት ቦታ በሙሉ የፖለቲካ መሠረት መጣልና አብዮታዊ ድርጅቶች ማቋቋም'' በሚለው መርሆ ስር ሰፊ ቅስቀሳ ይደረጋል:: በዚህ አንፃር አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ደረጃ ነን ለማለት ይቻላል::

ይህ ከሆነ በኋላ ለፖለቲካ ቅስቀሳውና የማደራጀት ተግባር ቅድሚያ በመስጠት ወታደራዊ ቅስቀሳ ማካሄድ መጀመር ይቻላል:: እንደየሁኔታው በሚያመቹ ቦታዎች በገለጽም ሆነ በስውር ወታደራዊ አካሎች እያቋቋሙ የፖለቲካ ቅስቀሳውን በሰፊው መቀጠል በዚህ ትግል ደረጃ እንደ ከፍተኛ ተግባር መቆጠር አለበት::

የ.ተወሰኑ ሰፈራዎችን በአብዮታዊ ኃይሎች ሙሉ ቁጥጥር ስር የዋሉ ሰፈራዎች መኖር ለጦር ትግሉ መቀጠል እጅግ አስፈላጊ ነው:: ከነዚህ ሰፈሮች በመነሳት በጠላት ቁጥጥር ስር ባሉት ቦታዎች የገሪላ ትግል ለማስፋፋትም ሆነ፣ ለሕዝባዊ ሠራዊቱ መጠለያ ሰፈራዎች ለማቋቋምና ሰራዊቱን ለመቀለብ.....ወዘተ የነዚህ ነፃ የወጡ ሰፈራዎች መኖር ምን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ ለመረዳት አያስቸግርም::

አንዱ ጊዜ ከጠላት ቁጥጥር ውጭ የሆኑትን ሰፈራዎች መልሶ ላለማስነጠቅ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል:: ወዲያውኑ በነዚህ ሰፈራዎች የግንባሩን ብሄራዊ ዲሞክራቲክ ፕሮግራም በስራ ላይ በማዋል፣ የቆየውን ሥርዓት በመበስበስና ያዲሱን ሕዝባዊ ስርዓት ጠቃሚነት ለሰፊው ሕዝብ ማሳየትም ፍፁም መዘንጋት የሌለበት ተቀዳሚ ተግባር ነው::

ይህን ተግባር በሚገባ መፈጸም ሰፊው ሕዝብ ለአብዮት ያለውን ስሜት ከማጠንከሩም በላይ በጠላት አስተዳደር ስር ያሉት ያካባቢው ሕዝቦች በጠላት ላይ እንዲነሱ ይረዳል:: ብሎም በነዚሁ ነፃ በወጡ ስፍራዎች አካባቢ በሚገኙት ቦታዎች ሰፊ የፖለቲካ ቅስቀሳ በማድረግ የጠላትን ሰፈር መበርበርና የገሪላውን ውጊያ በጠላት ሰፈር ማስፋፋት ይቻላል ማለት ነው::

ለ/ <u>በገጠር ነፃ የወጡትን ስፍራዎች ማጠናከር ብሎም በገጠር ጠንካራ መሠረት መጣልና በከተማ አብዮታዊ እንቅስቃሴውን ማፋፋም::</u>

በአብዮታዊ ትግሉ ጥቅሙ የሚጠበቅበት የሕዝቡ 90 % የሚሆነው ገበሬ የሚገኘው በገጠር እንደመሆኑ መጠን ገጠሩ ለአብዮታዊ ኃይሎች የማይናቅ የኃይል ምንጭ ነው:: ከዚያም አልፎ የጦር ትግል ለማንቀሳቀስም ሆነ ለማስፋፋት ገጠር አመቺ ቦታ ነው:: የጠላት ኃይል በገጠር ሙሉ ቁጥጥር ለማዋል በቂ ችሎታ ስለሌለው ከከተማ ይልቅ ገጠር ብዙ ድካም ይታይበታል:: በተጨማሪ ገጠሩ ራሱን በራሱ ሊቀልብና ሊያስተዳድር ይችላል::

ስለ ቬየትናምም ሆነ ስለ ቻይና የፀፋ አብዮታውያን እንደሚያስቡት በተለይ ጋራማ ስፍራዎች ከፍተኛ "ስትራቴጂካል ኢንፖርታንስ" አላቸው:: እነዚህን ስፍራዎች ነፃ በማውጣት ሕዝባዊ ሠራዊቱ ለሚያካሂደው ረጅምና መራራ ትግል ጠንካራ ድጋፍ መስጠት ይቻላል::ከዚያም በመነሳት ባካባቢው ባሉት ሜዳማ ስፍራዎች ጠላትን ማጥቃትና በአብዮታዊያን ቁጥጥር ስር የዋሉ ስፍራዎች ለማስፋፋት ይቻላል::

ባጠቃላይ ደረጃ አብዮታውያን ገጠሩን ነፃ ሲያወጡ፣ ለሕዝባዊ ሠራዊቱ በቁጥር ከፍተኛ የሆኑ ወታደሮች ሊያሰልፍ ከመቻላቸውም በላይ ከገጠሩ የሚያገኙትን ምርት ለአብዮታዊ ትግሉ ሊያውሉ ይችላል፣ ሠራዊቱንም ይቀልብበታል:: ከገጠርም በመነሳት ባካባቢው በሚገኙ ከተማዎች የሚካሄደውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሊደግፍና ጠላት የተጠራቀመባቸውን ከተሞች ሊያጠቃ ይችላል:: ይህንንም በማድረግ ጠላትን ክፉ ቦታ ይመታዋል ማለት ነው::

አብዮታውያን ከገጠር ነፃ ያወጡዋቸውን ስፍራ በሚያጠናክሩበት ጊዜ ባካባቢው በሚገኙ ከተሞች አብዮታዊ እንቅስቃሴውን ለማፋፋም ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለባቸው::

ለአብዮቱ ከተሰለፉ መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ከሁሉ አብዮታዊና ቆራጥ የሆነው የወዛደር መደብ የሚገኘው በከተሞች ነው:: ከዚያም አልፎ ለአብዮቱ የቆሙ የሕብረተሰብ ክፍሎች /ተማሪዎች አብዮታዊ ምሁራን ልዩ ልዩ የንዑስ ከበርቴ ክፍሎች/ በከተማ ይገኛሉ::



ጠላት ኃይሉን የሚሰበስበው በከተሞች በተለይም በትላልቅ ከተሞች በመሆኑ ከገጠር ይልቅ በከተማ ኃይለኛ ይሆናል:: በተለይ የከተማ ኢንዱስትሪዎችን በቁጥጥሩ ስር በማዋል ለሚካሄደው ፀረ ሕዝብ ጦርነት የኢኮኖሚ ድጋፍ የሚያገኘው ከከተሞች ነው:: ስለዚህም የፀረ አብዮት ኃይሎች ከተማውን ዋና የጦር ሰፈራቸው ሊያደርጉት ይሞክራሉ:: ይሁንናም በከተማ የጠላት ሠፈር በሚሊተሪም ሆነ በተለይ በፖለቲካ በኩል ብዙ ድካሞች አሉበት:: እንግዲህ በከተማ የፀረ አብዮት ኃይሎች እንዳይደላደሉ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ማለት ነው:: ይህም ሊሆን የሚችለው አብዮታውያን በገጠር ነፃ ያወጡትን ስፍራዎች አጠናክረው በከተማ የፀረ አብዮት ኃይሎች ያላቸውን የፖለቲካ ድጋፍ ለማመንመን ሰፊውን የከተማ ሕዝብ በተለይም ወዛደሩን በማነሳሳትና ባጠቃላይ ደረጃ የከተማውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ በማፋፋም ይሆናል:: ሁኔታው አመቺ ከሆነ ከተሞችንም ነፃ ማውጣት ቢቻል በአብዮታውያን ቁጥጥር ስር ያሉትን ስፍራዎች ማስፋፋት ይቻላል ማለት ነው:: ብሎም ያገሪቱን አንዱ ክፍል በአብዮታዊ ኃይሎች አስተዳደር ስር ማዋል ይቻላል ማለት ነው::

የቬየትናም ምሳሌ እንደሚያሳየን፣ የቬየትናም አብዮታውያን ይህን የመሰለ ትግል ካካሄዱ በኋላ ዲን ቢን ፊው ላይ ድል ከተቀዳጁ በኋላ መላ ሰሜኑን ነፃ አውጥተው በሰሜን ቬየትናም ነፃ የሆነ ሶሺያሊስት መንግሥት ለማቋቋም ችለዋል::

በሕዝባዊ ጦርነት ወደፊት መራመድ የሚቻለው ነፃ ያወጡትን ስፍራ እያጠናከሩ የጠላትን ሠፈር ወደ ጦር ሜዳ በመለወጥ ነው:: የሕዝባዊ ሠራዊትም ከዚህ ጋር ያድጋል፣ በሕዝባዊ ሚሊሻዎችና በጉሬላ ተዋጊ ቡድኖች መወሰን አልፎ ያካባቢ ሠራዊቶች ከዚያም መደበኛ ሠራዊቶች /የምድር ጦር የአየር ኃይል የባህር ኃይል/ እያደጉና እያደገ ይመጣል ማለት ነው:: በዚህ መልክም ሕዝባዊ ጦርነቱ እያደገ ይሄዳል::

ግን አሁንም ማስገንዘብ የሚያስፈልገው በያንዳንዱ ደረጃ የጦር ትግሉና የፖለቲካ ትግሉ የጦር ኃይሉና የፖለቲካ ድርጅቶች ፍፁም ባንድነት እንደሚራመዱና፣ ሕዝባዊ አብዮታዊ ግንባሩም ሆነ ሕዝባዊ ሠራዊቱ በወዛደሩ ፓርቲ አመራር ስር እንደሚራመዱ ነው::

ሕዝባዊ ጦርነት ረጅምና መራራ ጦርነት ነው:: ስለዚህም በማያቋርጥ ሁኔታ ከጠላት ጋር በከተማም ሆነ በገጠር የሚደረግ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ትግል ነው:: ጠላት በተሸነፈ ቁጥር በተገኘው ድል ተጠቅሞ የራስን ኃይል ማጠናከርን ይጠይቃል:: ጦርነቱ በተራመደ ቁጥርም ሰፊው ሕዝብ የሚቀዳጃቸው ድሎች እያደጉ እንጂ እየመነመኑ እንዳይሄዱ ማድረግም አስፈላጊ ነው::

ስለዚህም ሕዝባዊ ጦርነት ባጠቃላይ ሲታይ በማያቋርጥ ሁኔታ በአጥቂነት መገኘት አለበት:: ባንዳንድ ቦታዎች ወደ ኋላ ማፈግፈግ ቢያስፈልግም በይበልጥ አመቺ በሆነ ሁኔታ ለማጥቃት እንዲቻል እንጂ ሕዝባዊ ጦርነትን ወደ ተከላካይነት ወጥመድ ለመጠመር መሆን የለበትም::

ያለ ማቋረጥ ጠላትን በገጠርም በከተማም ማጥቃት፣ በፖለቲካ ትግል ማዳከም በወታደራዊ ትግል የጠላትን ኃይል መደምሰስና ተስፋ ማስቆረጥ የትግሉ መስመር እንዲሆን ያስፈልጋል:: የፖለቲካና ወታደራዊ ትግሉ ዋና የትግል መስክ ይሁኑ እንጂ በኢኮኖሚ በካልቸር.....ወዘተ ጠላትን በየቦታው ማዳከምና ሕዝቡን በነዚህ ጥያቄዎችም ጭምር ማነሳሳት ያስፈልጋል::

አብዮታዊ ትግሉ በዚህ መልክ በአጥቂነት ከተካሄደ ነፃ የወጡት ስፍራዎች የሚጠናከሩበትን ብሎም በጠላት ሥር ያሉትን ስፍራዎች ለማጥቃትና ነፃ ለማውጣት፣ የሚቻልበትን፣ በዚህም መንገድ በአብዮታውያን ቁጥጥር ስር ያልዋለውን ስፍራ የሚስፋፋበትን ሁኔታ ለመፍጠር ይቻላል:: በዚህ መንገድ፣ የጠላትን ስትራቴጂ እያከሸፉ በድል ላይ ድል በመደመር እስከመጨረሻው ድል መራመድ ይቻላል ማለት ነው::

ይህ ሲሆን ግን ምንጊዜም ሕዝባዊ ጦርነቱ ረጅምና መራራ መሆኑን መዘንጋት አያስፈልግም:: ስለዚህም ጠላትን በየመስኩ እያጠቁ የራስን ኃይል ግን መሰብሰብ፣ ነፃ የወጡትን አካባቢዎች ማለማትና ማጠናከር፣ ብሎም ለረጅምና ለመራራ ትግል አስፈላጊ የሆነው የሰውም ሆነ የማቴርያል ኃይል የሚዳብርበትን መንገድ መተለም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ተግባር ነው::

5. <u>ወታደራዊ ስልት</u>

በሕዝባዊ ጦርነት ውስጥ ወታደራዊ ስልት ከፍተኛ ቦታ አለው:: የሕዝባዊ ጦርነት የጦር ስልት ከሕዝባዊ ጦርነት መሰረታዊ መመርያዎች ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው::

በሕዝባዊ ጦርነት ውስጥ በስትራቴጂ በታክቲክና "ኦፐሬሽናል አርት" ማሀል ያሉትን ግንኙነቶች የሚወስነው ይህ ወታደራዊ ስልት ነው:: ስትራቴጂ የጦርነቱ ዋና መመሪያ ቢሆን ትክክለኛ ስትራቴጂ ለልዩ ልዩ "ኦፐሬሽን" ኖችና መካሄት አመቺ ሁኔታ ይፈጥራል:: ለልዩ ልዩ "ኦፐሬሽን" ኖች መካሄትና የወታደራዊ ታክቲኮች በትክክል ሥራ ላይ መዋል፣ የስትራቴጂውን ግቡን ለመምታት ያስችላል::



ሀ/ <u>የሕዝባዊ ጦርነት ሕዝባዊ ስልት መላውን ሕዝብ ለጦርነቱ የሚያሰልፍ ወታደራዊ ስልት መሆን አለበት::</u>

ጭቁን መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ወንዱ፣ሴቱ፣ወጣቱ፣ሽማግሌው፣የልዩ ልዩ ብሄረሰቦችና ሃይማኖቶች ጭቁን ሕዝቦች በአንድነት ጠላትን ለመደምሰስ እንዲነሱ፣ጠመንጃ ያለው ጠመንጃውን ይዞ፣ዱላ ያለው ዱላውን ይዞ፣ምንም መሣሪያ የሌለው ቱላውንም ቢሆን ይዞ በጠላት ላይ የሚነሳበት ሁኔታ እንዲፈጠር፣የሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት ይቀየሳል::በወዛደሩ ፓርቲ ስር ያለው ወታደራዊ አመራር፣የመላ ሕዝባዊ ሠራዊቱን ወታደራዊ ተግባሮችም ሆነ የመላውን ሕዝብ ወታደራዊ ትግል የሚያቀነባብር ወታደራዊ ስልት ይቀይሳል::የጠላትን በፈር በሚያዳክምበት ጊዜ ወታደራዊ አመራሩ፣ያለማቋረጥ የሰፊው ሕዝብ የፖለቲካ ትግል እንዲፋፋም ሰፊው ሕዝብ በልዩ ልዩ ጥያቄዎች ላይ እንዲነሳሳ፣በጠላት ሠራዊት ውስጥ ጭምር ስራ ቅስቀሳ የሚያካሄድበትን ሁኔታ ይፈጥራል::ስለሆነም ወታደራዊ ስልቱ በሚቀየርበት ጊዜ ያካባቢውን የፖለቲካ ትግል እንዳያቃውሰው መጠንቀቅ አለባቸው::

ባጠቃላይ ሲታይ የሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት የጦር ትግሉንና የፖለቲካ ትግሉን እያቀናበረ፣የጠላት በፈርን እያጠቃላውን ሕዝብ በየቦታው በጠላት ላይ እንዲነሳ አመቺ ሁኔታ የሚፈጥር ወታደራዊ ስልት ይሆናል::በተጨባጭ የሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት፣የጦር ትግሉ ምሰሶ የሆኑትን የሕዝባዊ ሠራዊቱን ሶስት አካሉች ያቀነባብራል::በሌላ አነጋገር "ሬጉላር" ሠራዊቱና ያካባቢ ሠራዊቱ የሚያካሂዱቸውን ትላልቅ ውጊያዎች ሕዝባዊ ሚሊሺያዎችን የጉሬላ ተዋጊዎች ከሚያካሂዱቸው አነስተኛ "ኦፐሬሽኖች" ጋር ያቀነባብራል ማለት ነው::

ለ/ <u>የሕዝባዊ ጦርነትን ወታደራዊ ስልት አይነተኛ የሚያደርገው ሁለተኛ ነጥብ የአጥቂነት ስትራቴጂ መከተሉ ነው::</u>

በሕዝባዊ የጦር ትግል ውስጥ ጠላትን በየቦታው በተገኘው መሣሪያ በልዩ ልዩ የማጥቂያ ዘዴዎችና በማንኛውም ጊዜ ያለማቋረጥና በታታሪነት ለማጥቃት ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል::

የህዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት ሕዝባዊ ሠራዊቱንና መላውን ሕዝብ ለጦርነት ለማሰለፍ፣አመቺ በሆኑት ሁኔታዎች በሙሉ እየተጠቀሙ፣የጠላትን ደካማ ወገን ለማጥቃት፣ብሎም በጠላትና በአብዮቱ በፈር ያለውን የሃይል አሰላለፍ ለአብዮታዊያን አመቺ እንዲሆን ለማድረግና በጦር ሜዳው በሙሉ ጠላትን

ወደ ተከላካይነት ለመከተት ያለማቋረጥ ጥረት ማድረግ ይኖርበታል:: ይህ ማለት በተወሰነ ቦታና ጊዜ ሕዝባዊ ትግሉ ወደ ተከላካይነት አይገባም ማለት አይደለም:: ሆኖም ባጠቃላይ ሲታይ ስትራቴጂው የአጥቂነት ስትራቴጂ መሆን አለበት ማለት ነው:: አንዳንዱ ጊዜና ባንዳንዱ ቦታ ወደ ተከላካይነት መሸጋሸግ ቢያስፈልግ እንደገና በተሻለ ሁኔታ ለማጥቃት እንዲቻል መሆን አለበት:: በሌላ አነጋገር ወደ ተከላካይነት በሚሸጋገበት ጊዜ፣ መመሪያው ""ማሸገሸግ በተሻለ ሁኔታ ለማጥቃት"" የሚለው መሆን አለበት ስለሆነም ሠራዊቱም ሆነ ማገናውም የሠራዊቱ አካል ወደ ኋላ ሲያሸገሽግ በቅልጥፍና በት ጋት፣ ሁልጊዜም መልሶ ለማጥቃት በመዘጋጀት ነው::

በዚህ የአጥቂነት ስትራቴጂ በመጠቀም፣ ወታደራዊ ስልቱ፣ የመላውን ሕዝብ ብርታትና የትግል ዘዴዎች እንዲሁም በፖለቲካ ደረጃ የአብዮቱ ሰፈር ያለውን ብልጫ ሕዝባዊ ጦርነቱ እንዲገለገልበት ሆኖ መቀየስ ይኖርበታል:: ""ያለማቋረጥ አብዮታዊ ንቃትን ከፍ እያደረገ፣ የሰው ቆራጥነትና እውቀት የተቻለውን ያህል እንዲዳብር በማድረግ፣ በሰውና በመሳሪያ ማሀል ያለውን ግንኙነት በትክክል በመፍታት፣ ለሰው ኃይል ለፖለቲካና ለሞራል ቅድሚያ በመስጠት፣ የትጥቅ የማቴሪያልና የቴክኒኩን ጥያቄ ሳይዘነጋ፣ ወታደራዊ ስልታችን ለሠራዊታችንና ለሕዝባችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄድ ቅልጥፍናና የአጥቂነት ችሎታ ሰቶስጠዋል::"" ጄኔራል ጂያፕ

ሐ/ <u>የሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት ደካማና ኃይለኛውን ሊያሸንፍ የሚችል በትን ሁኔታ የሚፈጥር መሆን አለበት::</u>

አንዱ ሕዝብ ነፃነቱን ለመቀዳጀት መሣሪያ ይዞ በሚነሳበት ሰዓት ብዙውን ጊዜ በተለይ በትጥቅ ደረጃ ከጠላት ሲነፃፀር ደካማ ነው:: ለምሳሌ በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ብንመለከት በማያሻማ ሁኔታ የፀረ አብዮቱ ሰፈር ከአብዮቱ ሰፈር ይበልጥ የታጠቀና የተዘጋጀ ነው::እንግዲህ ይህን የኃይል አሰላለፍ ቀይሮ ድልን ለመቀዳጀት የረቀቀ ወታደራዊ ስልት ይጠይቃል ማለት ነው:: እርግጥ ለዚህ ጥያቄ መሠረታዊ መልሱ የወታደራዊ ስልት ጥያቄ ሳይሆን ራሱ የሕዝባዊ ጦርነት ታሪካዊ ይዘት ነው:: ከፍ ብለን እንደተመለከ ትነው፣ ሕዝባዊ ጦርነት ለሕዝብ ጥቅም ለነፃነትና ለዴሞክራሲ የሚካሄድ ጦር ነት እንደመሆኑ መጠን በሰፊው ሕዝብ ስለሚደገፍና ስለሚታቀፍ ከጊዜ ብዛት በመሳሪያ ብልጫ ያለውን የጠላት ሰራዊት ሊያዳክምና ሊረታምና በመራራ የጦር ትግል ብርግጥ አሸናፊ ሆኖ ይወጣል:: ሊቀመንበር ማኦ እንዳሉት ""በጦ ርነቱ ልዩ ልዩ ደረጃዎች ትክክለኛ ወታደራዊና ፖለቲካዊ ታክቲክ ከተከተልን መሠረታዊ ስህተቶች ካልፈጸምን በተቻለ መጠን ኃይላችንን ሁሉ ከተጠቀምንበት ለኛ አመቺ የሆኑትና ለጠላት የማይመቹት ሁኔታዎች እየተጠናከሩ ይመጣሉ::



ይኸም ጠላት ኃይለኛ፡ እኛ ደካማ፣ ጠላት አሸናፊ፡ እኛ ተሸናፊ የነበርንበትን የመነሻ ሁኔታ ይቀይረውና በሌላ የትግል ደረጃ ሁኔታው በመሰረቱ ይቀየራል:: የዚህም ለውጥ ውጤቱ የኛን መሸነፍና የቻይና ማሸነፍ ይሆናል::

ግን እንግዲህ ራሱ የሊቀመንበር ማኦ ጥቅስ እንደሚያመለክተን ወታ ደራዊ ስልት በዚህ ደረጃ የማይናቅ ቦታ ይይዛል ማለት ነው:: ጠላት ተጋ ልጦ በሚገኝባቸው ቦታዎች ኃይልን መሰብሰብ፣ ፍጥነት ቅልጥፍና በድንገት መምታት፣ ባጠቃላይ ደረጃ የጠላት ኃይል ከፍተኛ ቢሆን በተወሰነ ቦታና በተወ ሰነ ጊዜ የበላይነት ይገኝ ዘንድ፣ በዚ ቦታና በዚን ጊዜ ሠራዊትን መሰብሰብ ብሎም ትንንሽ ድሎች በመቀዳጀት የጠላትን ኃይል መበርበርና የራስን ሰፈር ማጠ ናከር፣ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ግን ስትራቴጂካል ዓላማውን ሳይዘነጉ፣ በተቻለ መጠን ነፃ የወጡትን ስፍራዎች መልሶ ላለማስነጠቅና የሰውና የማቴሪያል ኃይል ላለማጥፋት መጠንቀቅ፣ ውጊያውን በየቦታው ማቀጣጠል፣ አያንዳንዱ እንቅስቃሴ የወዛደሩ ፓርቲ ወታደራዊ አመራር በቀየሰው መስመር ስር እንዲካሄድ ማድረግ .....ወዘተ ኃይለኛ ጠላትን ከደካማ ኃይል ተነስቶ ከጊዜ ብዛት ማዳከም የሚ ቻለው "" ለኛ አመቺና ለጠላት የማይመቹትን ሁኔታዎች ማጠናከር"" የሚቻለው በንደዚህ ዓይነት ወታደራዊ ስልት ነው:: የጠላትን ሠራዊት የጦር መሳሪያና መጠለያ ማጥቃት እጅግ አስፈላጊ ነው:: ሠራዊቱን በልዩ ልዩ የውጊያ ዘዴ መደምሰስ፣ የጦር መሣሪያውን መውረስና መጠለያውን /ለምሳሌ ከተሞችን/ከው ስጥ መበርበር፣ የፖለቲካና ወታደራዊ ድጋፍ በሚያገኝበት ቦታ የፖለቲካ ቅስ ቀሳ በማካሄድ በጠላት ሰፈር ሽብርን መፍጠርም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ተግ ባር ነው::

የሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት በሚቀየስበት ጊዜ፣ ኃይለኛ ጠላትን ከደካማ ኃይል ተነስቶ ለማሸነፍ፣ በሚስጥር መንቀሳቀስ አስፈላጊነትና በድንገት መምታት ጠቃሚነት ምንጊዜም መዘንጋት የለበትም::

እንግዲህ በ ሀ/ ለ/ ሐ/ ክፍል የተዘረዘሩትን የወታደራዊ ስልት መመሪያዎች በመከተል፣ በጦርነቱ ስትራቴጂካል ግቡና በያንዳንዱ "ኦፕሬሽን"ና ጊዜአዊ ታክቲክ ማሀል ያለውን ግኑኝነት በሕዝባዊ ሰራዊቱ ልዩ ልዩ አካሎች ማሀል ያለውን ግንኙነት፣ በተለያዩ የጦርነት አይነቶች ማሀል ያለውን ግን ኙነት መፍታት ይቻላል ማለት ነው::

1. <u>ከሁሉ አስቀድሞ በሶስቱ የሕዝባዊ ሰራዊት አካሎች የሚያካሄዱት ትግል እያደገ እንዲሄድ ጉሪላ ውጊያውና መደበኛ ሕዝባዊ ጦርነቱን በተቀናበረ መልክ ማካሄድ፣</u> ጉሪላ ውጊያውና መደበኛ ሕዝባዊ ጦርነትን በተቀናበረ መልክ ማካሄድ ሰፊውን ሕዝብ በሙሉ በሕዝባዊ ጦርነት ለማሰለፍ በሚደረገው ትግል መሠረታዊና ከፍተኛ ቦታ ይይዛል::

የገሪላ ውጊያ ሰፊው ሕዝብ በጦርነቱ የሚሳተፍበት የጦር ትግል አይነት ነው:: ጥቂት መደቦችና የሕብረተሰብ ክፍሎች ጠላትን በራሱ ሜዳ ላይ ጠለቀው በየሰፍራው ተሰማርተው የሚዋጉት በገሪላ ውጊያ በመጠቀም ነው:: የገሪላ ውጊያ ጠላትን በመበርበርና ከውስጥ በማዳከም፣ የጠላትን ኃይል በመከፋፈልና የጠላትን ስትራቴጂ በማፋለስ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: የገሪላ ውጊያ አይነተኛ አብዮታዊ ይዘት፣ ሰፊው ሕዝብ በአብዮታዊ አመጽ ተነስቶ በተወሰኑ ቦታዎች አመጽ /Insurrection/ በማነሳሳት ከታች የሰፊው ሕዝብ የስልጣን መሠረቶችን ለመገንባት ይጠቀማል::

አንድ ሕዝባዊ ጦርነት ሲጀምር ያለው ሠራዊት በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ የሚጀምረው በገሪላ ውጊያ ነው:: ገሪላውን በማስፋፋት በአካባቢ ሠራዊቶች አሳኛ ጠንካራ መደበኛ ሕዝባዊ ሠራዊት ይገነባል:: በሌላ ከገሪላ ውጊያ ወደ መደበኛ ሕዝባዊ ጦርነት መተላለፍ ይቻላል ማለት ነው::

ጄኔራል ቮን ጓያፕ ስለ መደበኛ ጦርነት ሲያትቱ እንዲህ ይላሉ::
•• የጠላትን ኃይል ለመደምሰስ ሰፊ ቦታዎችን ነፃ ለማውጣትና፣ የጦርነቱን በደረጃ በደረጃ ማሳደግ የሚያስችል ሁኔታ ፈጥሮ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ ድሎች ለመቀዳጀት የሚቻለው፣ መደበኛ ሰራዊቱ የልዩ ልዩ ክፍለ ጦሮችን ድርጊት እያቀነባበረ፣ ከአካባቢ ሠራዊቶች ከገሪላ ሚሊሻዎችና ከመላው ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር በመተባበር በሚያካሄደው መደበኛ ጦርነት ብቻ ነው::/ስርጉ የደራሰው/

በአብዮታዊ ጦርነት ውስጥ የገሪላ ውጊያ የመደበኛ ጦርነት መሠረት ይሆናል:: ገሪላ ውጊያው እንዲስፋፋና እንዲጠናከር መደበኛ ጦርነቱ ከገሪላ ውጊያው ጋር በጥብቅ የተቀነባበረ መሆን አለበት:: በተራውም የገሪላ ውጊያው መስፋፋት ለመደበኛ ጦርነቱ መንገዱን ይጠርጋል፣ አመቺ ሁኔታን ይፈጥራል::

ባጠቃላይ ደረጃ ሰበቱ የሕዝባዊ ሠራዊት አሃዶች አረማመዳቸውን ካቀነባበረ፣ ሁለቱ የውጊያ ዘዴዎች /ገሪላና መደበኛ ጦርነት/ እርስ በርስ ከተጋገዙና ከፖለቲካ ትግሉ እንዲሁም ከሌሎች ትግሎች ከተባበረ ሕዝባዊ ጦርነቱ በማያዳግም ሁኔታ ሊጠናከር ይችላል:: ከጦር ትግሉ አረማመድ ጋር የገሪላ ውጊያ ወደ መደበኛ ጦርነት እየተሸጋገረ ይመጣል::

2. የራስን ስትራቴጂካል እቅድ በጥሩ መንገድ መቀየስና፣ ጠላትን ወደማያዋጣ ስትራቴጂካል እቅድ ለመከተት ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል::



አሁንም ጄኔራል ጂያፕን እንጥቀስ::
•• ሕዝቡን በሙሉ ካሰለፍን፣ ጠላት በሰፈነባቸው ቦታዎች ጥምር ጠላትን የምንከበበትና በፖለቲካም ሆነ በሚሊተሪ ባጥቂነት የምንገኝበት ሁኔታ እንፈጥራለን:: ••

እንግዲህ ጠላትን የማያዋጣ ስትራቴጂካል እቅድ ውስጥ ለመከተት፣ መላውን ሕዝብ ማሰለፍ በልዩ ልዩ የትግል ዘዴዎች መጠቀም፣ በልዩ ልዩ የጦር ትግል መልክ መገለገል፣ በሌላ ለጠላት መተንፈሻ ጊዜ ባንሰጥ በአጥቂነት መታገል ይኖርብናል ማለት ነው:: ዋናው ነገር ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ወታደራዊ ስልቶቹንም ሆነ መሠረታዊ የሕዝባዊ ጦርነት መመሪያዎች በትክክል በሥራ ላይ በማዋል፣ ጠላት ተረጋግቶ የጦርነቱን አካሄድ ለሱ እንደሚመቸው አድርጎ እንዳይመራ ጊዜ መስጠት እንደማያስፈልግ መረዳት ነው:: በአንድ ሕዝባዊ ጦርነት ጠላትን በየቦታው እያዳከሙ የሚይዙትና የሚለቁትን ማሳጣት ለሕዝባዊ ጦርነቱ አካሄድ ወሳኝ የሚሆንበት ጊዜ ይመጣል::

3. የጥቃት እርምጃ የሚወሰድበት አቅጣጫና ጊዜ በሚገባ ተጠንቶ መወሰን አለበት::

በተወሰነ አቅጣጫ ማጥቃት ጊዜያዊ ድልን ለመቀዳጀት ሊጠቅም ይችላል:: ሆኖም ባጠቃላይ ሲታይ ወሳኝ ውጤት ላያመጣም ይችላል:: በተቻለ መጠን በስትራቴጂ ደረጃ ለውጥ ሊያመጣ የሚችልን አቅጣጫ መርጦ ማጥቃት ያዋጣል ማለት ነው:: የማጥቂያ ጊዜውን በሚለከተው በኩል፣ ጠላት የተዳከመበትን የተበታተነበትንና የማይጠባበቅበትን ጊዜ መርጦ ማጥቃት በጦር ትግሉ ትልቅ ቦታ ይይዛል::

4. የሕዝባዊ ሠራዊቱ ውጤት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ እንዲሄድና ሠራዊቱም በወታደራዊ ስልትና በፖለቲካ እየበሰለ እንዲሄድ መታገልም አስፈላጊ ነው::

በዓለም ሕዝቦች የአብዮት ታሪክ ውስጥ ትናንሽ አገሮች ሆነ በወታደራዊ ስልት ልምድ የሌላቸው ሕዝቦች በትጥቅም ሆነ በሠራዊት ብዛት ደካማ የሆኑ ሕዝባዊ ሠራዊቶች፣ ጠንካራና በዘመናዊ መሣሪያ የታጠቁን ኢምፔሪያሊስት አገሮች ድል መተዋል:: ሕዝባዊ ጦርነት በተራመደ ቁጥር የሕዝቡ ኃይል እየጨመረና የሕዝባዊ ሠራዊቱ ውጤት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ እያለ መሄዱም የብዙ ሕዝቦች የአብዮት ታሪክ ያስመሰከረው ሃቅ ነው::

ይህ ሊሆን የቻለበትም ምክንያት፣ አብዮታውያን በየጊዜውና በየቦታው የሕዝባዊ ጦርነትን መሠረታዊ አመራሮችና ወታደራዊ ስልት በሚገባ ሥራ ላይ ስላለዋሉት ነው:: የሕዝባዊ ሠራዊቱ ውጤት እያደገ እንዲሄድ መጣር ካጠቃላይ የጦርነቱ አመራር ውጤት እንዲሆንም ሁሉ፣ የሕዝባዊ ጦርነቱ አመራር ምን ጊዜም እንዲዘነጋው አያስፈልግም::

ለሕዝባዊ ጦርነቱ ከዱላ ወደ ዱላ መራመዱ፣ ለሰፊው ሕዝብ የትግል ፍላጐትና ቆራጥነት መጨመርና ለአብዮታዊ እንቅስቃሴው መቀጣጠል ከፍተኛና አይነተኛ ቦታ የሚይዝ ነጥብ ነው::

በዚህም ስለ ሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት ያደረግነውን ትንተና እናጠቃልላለን::

የሕዝባዊ ጦርነት ወታደራዊ ስልት፣ መላውን ሕዝብ ለጦርነቱ የሚያሰልፍ፣ በአጥቂነት ስትራቴጂ የሚመራ፣ ደካማ ኃይል በረዥምና በመራራ ትግል ኃይለኛውን የሚያሸንፍበት፣ በስትራቴጂና በታክቲክ በሕዝባዊ ሠራዊቱ ልዩ ልዩ አካሎች ማህል እንዲሁም ደግሞ በልዩ ልዩ የጦር ትግል አይነቶች ማህል ያሉትን ግንኙነቶች በሚገባ የሚፈታ ወታደራዊ ስልት ነው::



6. <u>በሠራዊት ውስጥ ሊወገዱ የሚገባቸው ስህተትና አዝማሚያዎች</u>

/ከሊቀመንበር ማኦ ትሴ ቱንግ ወታደራዊ ጽሑፎች ውስጥ የተገኘ
/ትርጉም የራሳችን/ /

<u>ፍፁም ወታደራዊያዊ የሆነ አዝማሚያ</u>

የቀዩ ሠራዊት አንዳንዱ ጓዶች ዘንድ ፍፁም ወታደራዊ የሆነ አዝማሚያ ይታያል:: የዚህ አዝማሚያ ምልክቶች የሚቀጥሉት ናቸው::

1. ፖለቲካና ሚሊተሪን በማቃረን ሚሊተሪ የፖለቲካ ተግባሮችን ለመፈጸም ከሚያስችሉት ነገሮች አንዱ መሆኑን ለማመን አይፈለግም:: አንዳንዶቹ •• በሚሊተሪ በኩል ነገር ከተሳካ በፖለቲካም ረገድ ሊሳካ እንደማይችል ይናገራሉ:: ይህም አስከፊነቱ ሚሊተሪ ፖለቲካን ይመራዋል ብሎ እንደማመን ነው::

2. የቀዩን ሠራዊት ተግባር እንደ ነጭ ሠራዊት ሁሉ ጦርነት ማካሄድ ብቻ ተደርጎ ይገመታል:: የቻይና ቀዩ ሠራዊት የአብዮቱን የፖለቲካ ተግባሮች ለመፈጸም የተደራጀ የታጠቀ ድርጅት መሆኑን አንረዳም:: በተለይ ባሁኑ ወቅት ቀዩ ሠራዊት በወታደራዊ ተግባሮች ብቻ አይወሰንም:: የጠላትን ወታደራዊ ኃይሎች ለመደምሰስ ከሚያካሂደው ጦርነት ሌላ፣ ቀዩ ሠራዊት ብዙ ዋና ዋና ተግባሮች አሉት፣ ማለትም በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ቅስቀሳ ማካሄድ፣ ሰፊውን ሕዝብ ማደራጀት፣ ሰፊውን ሕዝብ ማስታጠቅ አብዮታዊ ስልጣንን ለመመስረት የኮሚኒስት ፓርቲውን ድርጅቶች ለማቋቋም ጭምር ሰፊውን ሕዝብ ማገዝ አለበት ማለት ነው:: ቀዩ ሠራዊት ለጦርነት ብሎ ጦርነት አያካሂድም፣ ጦርነት የሚያካሂደው፣ በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ቅስቀሳ ለማድረግ፣ ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀት ሰፊውን ሕዝብ ለማስታጠቅና አብዮታዊ ስልጣን እንዲመሰርት ሰፊውን ሕዝብ ለማገዝ ብሎ ነው:: ያለነዚህ አላማዎች፣ ጦርነቱ ትርጉም አይኖረውም፣ የቀዩ ሰራዊትም ሕልውና ሊኖረው አይችልም::

3. ከዚህም ተነስተን፣ በድርጅት ጥያቄ በሠራዊቱ ውስጥ የፖለቲካ ተግባር የሚፈጽሙት አካሎች ወታደራዊ ተግባር በሚፈጽሙት አካሎች ታዛዥነት ሥር እንዲሆኑ እናደርጋለን:: ብሎም •• የኤታ ማዦርን ስልጣን እስከ ሠራዊቱ የውጭ ተግባሮች ድረስ ማስፋፋት •• የሚለውን መፈክር ይዞ መቅረብ ይመጣል:: እነዚህ አስተሳሰቦች ከተስፋፉ፣ ከሰፊው ሕዝብ የመገንጠል፣ ስልጣኑን በሠራዊቱ ቁጥጥር ሥር አድርጎ ከወዝደረ አመራር የማፈንገጥ ብሎም እንደ ኩሚንታንግ ሠራዊት ወደ ሚሊታሪዝም መንሰራራት አደጋ ይኖራል::

4. ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ በፕሮፓጋንዳ ደረጃ የፕሮፓጋንዳ ቡድኖችን ጠቃሚነት መከዳትና ሰፊውን ሕዝብ በማደራጀት አንፃር፣ በሠራዊቱ ውስጥ የወታደር ኮሚቴዎች ማቋቋሙንና፣ ያካባቢውን ወዛደርና አርሶ አደር ማደራጀቱን መዘንጋት ይመጣል:: ይህም የሚያስከትለው የፕሮፓጋንዳና የማደራጀቱ ተግባር ችላ ተብሎ መቅረቱን ነው::

5. ዱላ በተገኘ ቁጥር መሠረተ ቢስ ደስታና ዱላ በታጣ ቁጥር ተስፋ መቁረጥ::

6. ስለ ራስ ብቻ ማሰብ/ ፓር ቲኩላሪዝም / በማንኛውም ሁኔታ ስለ እራተኛው ክፍለ ጦር ብቻ ማሰብ ከቀዩ ሠራዊት ዋና ዋና ተግባሮች እንዱ ባካባቢው ያለውን ሕዝብ ማስታጠቅ መሆኑን መዘንጋት:: ይህም የቡድን ስሜት ከፍተኛ ደረጃው ነው::

7. ጥቂት ጓዶች እስተባሰባቸውን በአራተኛው ክፍለ ጦር ዘርፍ ብቻ በመወሰን ከነሱ ሌላ አብዮታዊ ኃይል ያለ አይመስላቸውም:: ስለዚህም፣ ኃይላቸውን የማንከባከብና፣ ማንኛውንም ተግባር ከማከናወን የሚቆጠብ አዝማሚያ ይታይባቸዋል:: ይህም የአድርባይነት ተቀጢላ ነው::

8. ነባራዊውንና ግላዊ / አብጀክቲቭና ሰብጀክቲቭ / ሁኔታዎችን አለመረዳት፣ ቸኩልነት
በሕዝቡ ዘንድ ትጋትን በሚጠይቅ፣ ውጤቱ በማይታይና በጥንቃቄ በሚሰራ ሥራ አለመሰማራት፣ ደብቆ ለመፈጸም የማለምና የምኞት ላይ የመመርኮዝ አዝማሚያ:: ይህ ሁሉ የፑቺዝም ተቀጢላ ነው::

ፍፁም ወታደራዊ የሆነ አዝማሚያ መሠረቶቹ የሚቀጥሉት ናቸው::

1. የፖለቲካ ንቃት ዝቅተኛነት:: በሎም በሠራዊት ውስጥ የፖለቲካ አመራርን አስፈላጊነት አለመረዳት፣ በነጭ ሠራዊትና በቀዩ ሠራዊት ማሀል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት አለማወቅ::

2. የቀጥረኛ ሠራዊት ዘለማዱ/ "ሜርሰኔሪ ትሬዲሽን ሜንታሊቲ" /:: ከውጊያዎች በኋላ የተያዙ የብዙ ምርኮኞች ከቀዩ ሠራዊት ጋር አለመዋሃድ፣ በሠራዊቱ ዝቅተኛ አካል ውስጥ ፍፁም ወታደራዊ የሆነ አዝማሚያ እንዲስፋፋ አመቺ ሁኔታ ፈጥረዋል::

3. በወታደራዊ ኃይል ላይ ወሰን የለሽ እምነት መጣልና በሰፊው ሕዝብ ላይ እምነት ማጣት:: ይህ ሦስተኛ ነጥብ ከሁለቱ ነጥቦች የሚመነጭ ነው::

4. አንዳንዱ ጓዶች ፍፁም ወታደራዊ የሆነ አዝማሚያ ሊያሳዩ የቻሉት፣ ፓርቲው በወታደራዊ ተግባሮች ላይ አስፈላጊውን እንክብካቤ ካለማሳየቱ በዚህ ተግባር ላይ አስፈላጊውን ውይይት ካለማካሄዱ ነው::



እነዚህን ስህተቶች ለማረም የሚቀጥሉትን ማሟላት ያስፈልጋል:-

1. ሰፊ ትምህርት በመስጠት የፓርቲውን አባሎች የፖለቲካ ንቃት ከፍ ማድረግ:: የዚህን ፍጹም ወታደራዊ የሆነ አዝማሚያ ቲኦረቲካል መሠረቶች መደምሰስና በቀዩ ሠራዊትና በነጭ ሠራዊት ማሀል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት በሚገባ ማሳየት:: ከዚሁ ጋር አያይዞ የአድርባይነትና የፑቺዝምን ተቀጢላዎች ማጥፋት፣ የ4ኛውን ክፍለ ጦር የቡድን ስሜት መስበር::

2. የመኮንኖችንና የሠራዊቱን የፖለቲካ ትምህርት በተለይም ለቀድሞ እሥረኞች /ምርኮኞች/ የሚሰጠውን ትምህርት ማጠናከር:: በሌላ በኩል ፍጹም ወታደራዊ የሆነውን አዝማሚያ ድርጅታዊ ሥረ መሠረቶች ለማዳከምና ቢቻልም እስከ ነጭራሹ ለማጥፋት፣ በትግል የታነፁ ወዛደሮችና አርሶ አደሮች በአካባቢው የሰለጠን አካሎች እየተመለመሉ በቀዩ ሠራዊት እንዲሰማሩ የተቻለውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል::

3. በአካባቢው ያሉ የፓርቲው ድርጅቶች በሠራዊት ውስጥ በተሰማሩ የፓርቲው ድርጅቶች ላይ ሂስ እንዲያቀርቡ፣ በሠራዊቱ የተሰማሩት የፓርቲው ድርጅቶች በሠራዊቱ መኮንኖችና ወታደሮች ላይ ጤናማ ተጽኖ ይኖር ዘንድ፣ የህዝባዊ ስልጣኑ አካሎች በቀዩ ሠራዊት ላይ ሂስ እንዲያቀርቡ ጥሪ ማድረግ::

4. ፓርቲው ወታደራዊ ተግባሮችን በእንክብካቤ መመልከትና በትጋት መመርመር አለበት:: ማንኛውም ተግባር በሕዝቡ ከመከናወኑ በፊት በፓርቲው ድርጅት ተመክሮበት የሚወሰን መሆን ይኖርበታል::

5. በወታደራዊ አካሎችና በፖለቲካ አካሎች ማሀል፣ በቀዩ ሠራዊትና በሰፊው ሕዝብ ማሀል ያለውን ግንኙነት፣ የወታደሮችን ኮሚቴዎች ችሎታና ከፖለቲካና ከወታደራዊ አካሎች ጋር ያላቸውን ግንኙነት በትክክል የሚወስኑ የቀዩን ሠራዊት ውስጣዊ ህጎችና ደንቦች መተለም::

<u>"አልትራ ዲሞክራቲዝም"/ Ultra-democratism</u> /

የቀዩ ሠራዊት አራተኛ ክፍለ ጦር በማዕከላዊ ኮሚቴው አመራር ስር ከዋለበት ጊዜ አንስቶ፣ በውስጡ ይታዩ የነበሩት የ "አልትራ ዲሞክራቲዝም" ምልክቶች ቀንሰዋል:: ለምሳሌ የፓርቲውን ውሳኔዎች በሥራ ለመተርጎም ቀለል ሊል የቻለው ከዚህ የተነሳ ነው:: "ከታች ወደ ላይ የሚሄድ ዲሞክራቲክ ሴንትራሊዝም" ወይም ደግሞ "በከፍተኛ ደረጃ ውሳኔ ከመውሰድ በፊት በዝቅተኛ ደረጃ ባሉ አባሎች ጥያቄው መመርመር አለበት" የተባሉትን መፈክሮች

በቀይ ሠራዊት ውስጥ በሥራ ላይ ይዋል የሚሉ አባባሎች መሰማት አቁዋል:: ይሁንና በተጨባጭ ሲታይ የ'አልትራ ግራ ዚዝም' መዳከም ጊዜያዊና ላይ ላዩን ነው::ይህን የመሰለ መገረስ ከነጥራሹ ጠፍቷል ለማለት አይቻልም::

በሌላ አነጋገር አሁንም በበዙ ጓዶች ዘንድ ስር ሰደዋል:: ለምሳሌ የፓርቲውን ውሳኔዎች በሥራ ለመተርጎም የሚታየው ለዘብተኛነት አንዱ ምስክር ነው::ይህን አዝማሚያ ለማጥፋት መፍትሄዎች የሚቀጥሉት ናቸው::

1. በቲዎሪ ደረጃ የ'አልትራ ግራ ዚዝም'ን ስረ መሠረቶች መደምሰስ ያስፈልጋል::ከሁሉ አስቀድሞ 'አልትራ ግራ ዚዝም' የፓርቲውን ድርጅቶች እንደሚበረዙና እስከማጥፋትም እንደሚደርስ፣የፓርቲውን የታጋይነት ችሎታ እንደሚያዳክምና እስከነጥራሹ ሊያመነምን እንደሚችል፣ስለዚህም በትግል ውስጥ ፓርቲው ተግባሮችን እንዳይፈፅም በሎም አብዮትን ወደ መሸነፍ እንደሚወስድ፣ በሚገባ ማስረዳት ያስፈልጋል::ከዚም፣ የ'አልትራ ግራ ዚዝም' ምንጭ የንዑስ ከበርቴ ፀረ ዲሲፕሊንነት መሆኑን ማስገንዘብ ጥሩ ነው::ይህም /የንዑስ ከበርቴው ፀረ ዲሲፕሊንነት/ በፓርቲው ውስጥ ሲስፋፋ ፍፁም ከወዛአደሩ የትግል ተግባሮች ጋር ሊጣጣም የማይችል የ'አልትራ ግራ ዚዝም'ን አሰራር ይወልዳል::

2. በድርጅት ደረጃ የሚቀጥሉት መመሪያዎች በመመስረት በማዕከላዊነት የሚመራ የዲሞክራሲ መርሆችን ሳያወላውሉ በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል::

- ሀ/ የፓርቲው መሪ አካሎች፣ትክክለኛ መመሪያ መተለም አለባቸው::ለሚነሱት ችግሮች መፍትሄ በማግኘት፣እንደ አመራር አንበርት ማገልገል ይኖርባቸዋል::
- ለ/ ለትክክለኛ አመራር ተጨባጭ መመርከዝ ይኖራቸው ዘንድ የበላይ አካሎች የበታች አካሎችን ሁኔታና የሰፊውን ሕዝብ ኑሮ በሚገባ ማወቅ አለባቸው::
- ሐ/ በልዩ ልዩ ደረጃ የሚገኙት የፓርቲው ድርጅታዊ አካሎች የሚወሰኑትን ውሳኔዎች በቀላሉ ማየት የለባቸውም::ውሳኔው አንዴ ከተላለፈ ወዲያ በቆራጥነት በሥራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል::
- መ/ በፓርቲው የበላይ አካል የሚወሰኑትን ዋና ዋና ውሳኔዎች በሙሉ የበታች አካሎችና ሰፊው የፓርቲው አባሎች በቶሎ እንዲያውቋቸው ማድረግ አለበት::ይህም ይሆን ዘንድ፣የአባሎችን ስብሰባ ወይንም የክበቦችን ጠቅላላ ስብሰባ ሁኔታው አመቺ ሲሆን፣የ'ኢኪዚዶችን' የፓርቲ አባሎች ስብሰባ ጥምር በመጥራት፣የተወደቡ ጓዶች ሪፖርት እንዲያደርጉ ያስፈልጋል::



- ሠ/ የፓርቲው የበታች አካሎችና ሰፊው የፓርቲ አባሎች የበላይ አካሎች በሚያወጧቸው መምሪያዎች ላይ ሰፊ ውይይት ማካሄድና ይዘቱን ተረድተው በሥራ የሚተረጎሙበትን መንገድ መተለም አለባቸው::

<u>ከፓርቲው ድርጅታዊ መርሆዎች ተፃራሪ የሆኑ ገፅታዎች</u>

በ4ተኛው ክፍለ ጦር የፓርቲ ድርጅቶች ውስጥ ከፓርቲው ድርጅታዊ መርሆዎች ተፃራሪ የሆኑ ገፅታዎች የሚስፋፉት እንደሚቀጥለው ነው::

- ሀ/ የማይኖሪቲው በበዙሃኑ ስር መሆኑን አለመቀበል፣ለምሳሌ የማይኖሪቲውን ሃሳቦች ተቀባይነት ሲያጡ የማይኖሪቲው ደጋፊዎች የፓርቲውን ውሳኔ በሥራ ለመተርጎም አይፈልጉም::የዚህ መፍትሄው :–

1. ያንዱ ስብሰባ ተሳታፊዎች ሃሳባቸውን ለማሰማት እድል እንዲሰጣቸው አስፈላጊውን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል::ለመጠጋገን ወይም እንዲያው ለይስሙላ መፍትሄ መፈለግ ሳይሆን ቀራኒ ባስነሱ ጥያቄዎች ላይ ትክክለኛውንና ስህተተኛውን በሚገባ መጠቆም ያስፈልጋል::ጥያቄው መፍትሄ ካላገኘ፣ሥራውን እንዳይጓተት ሆኖ እንደገና መመርመርና ትክክለኛ ውጤት ላይ መድረስ ያስፈልጋል::

2. ከፓርቲው የዲሲፕሊን ሕጎች አንዱ የማይኖሪቲው ለበዙሃኑ መታዘዝ ነው::የማይኖሪቲው ሃሳብ ተቀባይነት ሲያጣ ማይኖሪቲው በበዙሃኑ ውሳኔ ስር መሰለፍ አለበት::አስፈላጊ ከሆነ ጥያቄው በሌላ ስብሰባ መቅረብ ይችላል::ነገር ግን በምንም አይነት ውሳኔውን የሚፃረር እርምጃ መወሰድ የለበትም::

— ለ/ የድርጅታዊ መርሆችን የማይከተል ሂስ

1. በፓርቲው ውስጥ የሚደረግ ሂስ የፖርቲውን ድርጅቶች የሚያጠናክርና የፖርቲውን የትግል ችሎታ የሚያዳብር መሣሪያ ነው:: ይሁንና በቀይ ሠራዊት የፖርቲ ድርጅቶች ውስጥ አንዳንዱ ጊዜ ሂስ ሌላ መልክ ይዞ ይቀርባል:: ሂሱ ግላዊ መልክ ይይዛል:: ይህም በግለሰቦችም ብቻ ሳይሆን በፖርቲውም ድርጅቶች ላይም ጉዳት ያመጣል:: ይህም የንዑስ ከበርቴ ግላዊነትን / ኢንዲቪዲዋሊዝም / ያመለክታል:: የዚህም መፍትሔ የፖርቲው አባላት ሂስ በመደብ ትግል ውስጥ ዱላን እንዲንቀሳቀሱ ዘንድ የፖርቲውን የትግል ችሎታ የሚያዳብር መሣሪያ እንጂ፣ ግለ ሰብን ለማጥቃት የሚያገለግል መሣሪያ አለመሆኑን ማስረዳት ያስፈልጋል::

2. ብዙ የፖርቲ አባላት ሃሳቸውን ከፖርቲው ውጭ እንጂ በፖርቲው ውስጥ አያደርጉም:: ይህም ሊሆን የሚችለው ብዙው የፖርቲ አባላት የፖርቲውን ድርጅቶች ምንነት ስለማይረዱና፣ በፖርቲው ውስጥ በሚደረገው ሃሳና፣ ከፖርቲው ውጭ በሚደረገው ሃሳ መሐል ምንም ልዩነት ያለ ስለማይመስላቸው ነው:: የዚህም መፍትሔ የፖርቲው አባላት የፖርቲውን ድርጅቶች ምንነት ደረጃ ዘንድና ሃሳም በኮሚቴም ሆነ በጓዶች ላይ በሚያቀርቡበት ጊዜ በፖርቲው ስብሰባዎች ላይ ማቅረብ እንዳለባቸው ደረጃ ዘንድ አስፈላጊውን ትምህርት መስጠት ነው::

<u>የፍጹም አኩልነት ፈሊጥ /ስበበሊዩት ኢጋሊታሪዝም</u>

ባንዱ በተወሰነ ጊዜ የፍጹም አኩልነት ፈሊጥ በቀይ ሠራዊት ውስጥ አስጊ ደረጃ ደርሶ ነበር:: አንዳንድ ምሳሌዎች ለመጥቀስ ያህል ለቆሰሉ ወታደሮች አበል በተከፈለበት ጊዜ አንዳንድ ጓዶች ከፍተኛ ቁስል በደረሰባቸውና፣ መለስተኛ ቁስል በደረሰባቸው መሃል ምንም ልዩነት ባይደረግ እኩል አበል እንዲከፈላቸው ጠይቀው ነበር:: አንድ መኮንን በፈረስ የሄደ እንደሆነ፣ ለሥራው አስፈላጊ መሆኑን ባለመረዳት አንዳንዶች ይህ ልዩነት ለከት ይመስላቸዋል:: ስንቅ በሚታደልበት ጊዜ አንዳንድ ዩኒቶች / units / ካሉበት ልዩ ሁኔታ የተነሳ ከሌላ የበለጠ ስንቅ እንደሚያስፈልጋቸው ሳይገነዘቡ አንዳንድ ጓዶች ለሁሉም እኩል ስንቅ ይጠይቃሉ፣ ሬዞ በምናጓጉዝበት ጊዜ ትልቅ ሰውም ሆነ ሕፃን ደካማም ሆነ ጠንካራ ሁሉም እኩል እንዲሸከም ይፈልጋሉ::
ጦሩ በሚሰፍርበት ጊዜ ለሁሉም እኩል ቦታ እንዲሰጥ አመራሩን በሩ ያለ ቦታ ከተሰጠው የሰልብ ወርደብን ያወርዳሉ:: በሥራ ክፍፍል ጊዜ ሁሉም እኩል እንዲሠራና ማንም ከማንም በላይ አለሰራም ብሎ ይነሳል:: ለሁለት ቁስለኞች አንድ ማመላለሻ አልጋ ሲኖር፣ አንዱ ቁስለኛ ከሚጠቀምበት ማንም ባይጠቀምበት ይሻላቸዋል:: ይህም የሚያመለክተው በቀይ ሠራዊት መኮንኖችና ወታደሮች ዘንድ የፍፁም አኩልነት ፈሊጥ አሁንም ከፍተኛ ቦታ እንደሚይዝ ያመለክታል::

የፍፁም አኩልነት ፈሊጥና 'አልትራ ዲሞክራቲዝም'
ከፖለቲካ አንፃር ሲታይ ምንጫቸው አንድ ነው:: የ'ስሞል ስኬል ኢኮኖሚና የ'ስሞል ስኬል ፔዝንት ፕሮዳክሽን' ውጤቶች ናቸው:: በመሐላቸው ልዩነት አለ ሲባል አንደኛው በፖለቲካ መስክ ውስጥ የሚታይ ሲሆን፣ ሌላኛው በቀን ተቀን ኑሮ የሚታይ በመሆኑ ብቻ ነው::



የነዚህ አዝማሚያ መፍትሔዎች የፍፁም አኩልነት ፈሊጥ ትናንሽ ባለመሬቶች ካፒታሊዝም እስኪለተደመሰስ ድረስ የሚኖራቸው ምኞት ከመሆኑም በላይ በሀብረተሰባዊነትም ቢሆን የሐብት አደላደል " በያንዳንዱ እንደ ችሎታው ለያንዳንዱ እንደ ሥራው " በሚለው መርህ የሚመራና በሥራው አስፈላጊነት አንፃር የሚወሰን እንደመሆኑ መጠን የፍፁም አኩልነት ፈሊጥ በሀብረተሰባዊነት ቦታ እንደሌለው ማስገንዘብ ያስፈልጋል:: ቁሳቁሶች በቀዩ ሠራዊት አባላት መሐል ባጠቃላይ ደረጃ እኩል መደላደል አለባቸው፣ ለምሳሌ የወታደሮችና የመኮንኖች ደመወዝ እኩል መሆን አለበት ይህም ሊሆን የቻለው የትግላችን ጊዜያዊ ሁኔታ ስለሚያስገድደን ነው:: ሆኖም ግን ሌሎች ሁኔታዎችን የማይ ጨምር የፍፁም አኩልነት ፈሊጥን እንዲንታገለው ያስፈልጋል ምክንያቱም ትግሉ ለሚጠይቀው ተገቢውን መልስ አይሰጥም እንዲሁም ለትግሉ እንቅፋት ነው::

<u>ሰብጄክቲቪዝም /ስሜታዊነት/</u>

አንዳንዱ የፖርቲው አባላት በስሜታዊነት በከፍተኛ ደረጃ ተጠምቀዋል:: ይህም ተጨባጭ የፖለቲካ ሁኔታን ለመመርመርና ሥራውን መምራት አንፃር ብዙ ጉዳት ይጥላል:: በተጨባጩ ፖለቲካ ሁኔታ በሚታይ ትንተናና በስሜታዊነት የተጠመቀ የሥራ አመራር በግዱ ወደ አድርባይነትና ወደ ፑቲሽዝም ያመራል:: በስሜታዊነት የመረኮዙ ሃሳቦች መሠረት የሌላቸውና ከልክ በላይ የሚገነዘፉ አስተያየቶች፣ እንዲሁም ርስ በርስ መጠራጠር፣ ብዙውን ጊዜ ፖርቲው ውስጥ መረን የለቀቁ ልዩነቶች እንደሚያስከትሉ ሁሉ፣ የፖርቲውን ድርጅቶች ያቀረቅዛሉ::
በፖርቲው ውስጥ የሚካሄደውን ሃሳ በሚመለከተው በኩል ሌላ ነጥብ መጠቀስ አለበት፣ ማለትም አንዳንዱ ጓዶች ሃሳ በሚያደርጉበት ጊዜ በዋነኛው ነጥብ ላይ ከማተኮር ይልቅ በትርጉም የለሽ ነጥብ ላይ ያተኩራሉ::
የሃሳ ዋና አላማ የፖለቲካና የድርጅታዊ ስህተቶችን አስጥሮ ማውጣት እንደሆነ አይገነዘቡም:: የግለ ሰቦችን ጉድለት በሚመለከተው በኩል ከፖለቲካዊና ከድርጅታዊ ስህተቶች እስከሌተያያዙ ድረስ ጉዳዩን ሳላማስደንገጥ ያህል እነሱ ላይ ማተኮር አያስፈልገም:: እንዲሁም ደግሞ እንዲህ ዓይነት ሃሳቦች ከተስፋፉ የፓርቲውን ድርጅት በጥቃቅን ነገር ላይ እንዲያተኩር ያደርጋሉ፣ ጓዶችም የፖለቲካ ተግባሮች የሚዘነጉ ቀጥ ያሉ ሰዎች ይሆናሉ፣ ይህም ትልቅ አደጋ ነው::

እነዚህን ጉድለቶች ለማጥፋት ዋናው ነገር የፖርቲው አባላት አስተያየቶችና የፖርቲው ውስጣዊ ኑሮ ሳይንሳዊ የፖለቲካ አዝማሚያ ይይዙ ዘንድ የፖርቲውን አባላት ማስተማር ነው:: ይህም ይሆን ዘንድ 1/ የፖርቲው አባላት በስሜታዊነት የተጠመቀ ትንተናና ከማድረግ ይልቅ በማርክሲዝም ሌኒኒዝም ላይ የተመሰረተ የፖለቲካ ትንተናና የመደቦች አሰላለፍ ግምገማ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ትምህርት መስጠት፣ 2/ በኤኮኖሚና በሶሻል ደረጃ አስፈላጊውን ምርምርና ጥናት በማድረግና እነሱም ላይ በመመሥረት የትግሉን ታክቲክና የሥራውን ስልት መተለም አስፈላጊ መሆኑን ለፖርቲው አባላት ማስረዳት ያስፈልጋል:: ተጨባጩን ሁኔታ ካለመረመሩ ጓዶች በምኞትና በፑቲሽዝም

አዘቅት ውስጥ እንደሚወድቁ ማስገንዘብ ያስፈልጋል:: 3/ ፖርቲው ውስጥ ሂስ በሚደረግበት ጊዜ ጓዶች ከስሜታዊና ከመሠረተ ቢስ ግምቶች እንዲሁም ሂስን ከሚያቃልሉ አሠራሮች እንዲቆጠቡና የሚሰጡት አስተያየት መሠረት እንዲኖረውና ሂሳቸው የፖለቲካ ይዘት እንዲኖረው ያስፈልጋል::

ኢንዲቪዲዋሊዝም /ግለኝነት/

በቀይ ሠራዊት የፖርቲ ድርጅቶች ውስጥ የግለኝነት አዝማሚያ በሚቀጥሉ መልኮች ይታያል::

1. የብድር መለሽ መንፈስ:: ባንዱ ጓዱ ወይም ባንዱ የሠራዊት ወታደር ሂስ የቀረበበት የፖርቲው አባል ከፖርቲው ውጭ ብድሩን መመለስ ይፈልጋል:: "በበደበ ደበደበ.......ወዘተ ብድሩን ይመልሳል — እንዲሁም ደግሞ በፖርቲ ውስጥ ብድርን የመመለስ ፍላጎት አለ "ባለፈው ስብሰባ ሂስ አቀረብህብኛል በሚቀጥለው ስብሰባ ብድሬን ለመመለስ — ስህተት ፈልፍዬ አወጣብሃለሁ" ይህ ብድር የመመለስ መንፈስ በራስ ላይ ብቻ ከማተኮር የሚመጣ ነው:: የመላውን ፖርቲና የመደቡን ጥቅም አያይም:: ከመደብ ጠላቶቻችን ይልቅ ከመሰሎቻችን በሚገኙ ጓዶቻችን ላይ ያተኩራል:: የፖርቲውን ድርጅቶች እንደመርዝ የሚበርዙና የትግሉን ችሎታ የሚያዳክም ነው::

2. የቡድን ስሜት ለሁሉም ጥቅም ሳይሆን ለራሳችን ቡድን ጥቅም ብቻ መጨነቅ፣ የቡድን ስሜት ላይ ላዩን ሲታይ በግል ጥቅም ላይ ያልተመሠረተ ይመስላል፣ ነገር ግን ፍፁም ጠባብ በሆነ ግለኝነት ስሜት የሚታዘዝ ነው:: የቡድን ስሜት በቀዩ ሠራዊት ውስጥ ምን ጊዜም ቢሆን ነበር:: ወቀሳዎች ስለተደረጉ ሁኔታው በመጠኑ ተሻሽለዋል፣ ይሁንናም አሁንም የዚህ መንፈስ ምልክቶች አሉ:: ስለሆነም የቡድን ስሜትን ለማሸነፍ አዲስ ጥረቶች ማድረግ ያስፈልጋል::

3. የቅጥረኛ መንፈስ:: አንዳንዱ የፖርቲውና የቀዩ ሠራዊት አባሎች የሆኑ ጓዶች፣ ፖርቲውና ቀዩ ሠራዊቱ የአብዮቱን ተግባሮች ለማሟላት የሚያስፈልጉ መሣሪያዎች መሆናቸውን አይረዱም:: የአብዮቱ ዋና ዋና ኃይሎች እነሱ እንዲሆኑ አይገነዘቡም፣ ተጠያቂነታቸው ለአብዮቱ ሳይሆን ለመሪያቸው ይመስላቸዋል:: ይህ ዓይነቱ ቅጥረኛ መንፈስ በአብዮቱ አንፃር የግለኝነት ምልክት ነው:: ለአብዮቱ ባቀጥሙ ኃይላቸውን የሚለግሱ ንቁ ታጋዮች በብዛት የሌሉን ከዚሁ መንፈስ መኖር የተነሳ ነው:: ይህንን መንፈስ ካላደመሰስን የታጋዮቻችንን ቁጥር ሊያድግ አይችልም:: ስለሆነም የአብዮቱ ሸክሞች በጥቂት ጓዶች ትከሻ ላይ ይቀርና ለትግላችን ትልቅ ጉዳት ያመጣብናል::



4. የመደሰት ጉጉት:: በቀይ ሠራዊት ውስጥ ግለኝነታቸው በመደሰት ጉጉት የሚተረጎም ብዙ ናቸው:: ሠራዊታችን ወደ ትላልቅ ከተሞች እንዲሰማራ ይፈልጋሉ:: ይህም ለሥራ ሳይሆን ለመደሰት ነው:: የኑሮ ችግሮች ባሉባቸው ቀይ ስፍራዎች መሥራት ይቀፋቸዋል::

5. ዳተኛነትና ስንፍና:: አንዳንዶቹ፣ ሁኔታው እነሱ እንደሚፈልጉት ካልሆነላቸው ዳተኛ ይሆናሉ፣ ሥራ መሥራት አይፈልጉም:: ለዚህ መሠረታዊ ምክንያቱ የንቃት ጉድለት ነው:: ሆኖም ግን አንዳንዴ ጊዜ መሪዎች የልዩ ልዩ ጥያቄዎች መፍትሄዎችን በማግኘት በኩል፣ ሥራን በመከፋፈልና ስነስርዓትን በማስከበር ደረጃ ጉድለት ማሳየታቸው ለዚሁ ሁኔታ መነሻ ይሆናል::

6. ሠራዊቱን ለቆ የመሄድ ፍላጎት:: ከቀዩ ሠራዊት ለቀው ወደ ሲቪል ሥራ መሠማራት የሚፈልጉት ቁጥራቸው በያንዳንዱ ግለሰብ ምክንያት ብቻ ሳይሆን፣ የቀዩ ሠራዊት ቁሳቁሳዊ የኑሮ ሁኔታ በጣም መጥፎ በመሆኑ፣ ከረጅም ዓመታት ውጊያ በኋላ መዳከም ስለሚጀምሩ፣ መሪዎች የልዩ ልዩ ጥያቄዎች መፍትሄዎችን በማግኘት በኩል፣ ሥራን በማከፋፈል በሥርዓትን በማስከበር ደረጃ ጉድለት ስለሚያሳዩ ነው::

እነዚህን ጉድለቶች ለማረም::

በርዕዮተ ዓለም ደረጃ ግለኝነትን ለመደምሰስ የንቃት ደረጃውን ከፍ ማድረግ:: ከዚያም፣ ለሚነሱት ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ትክክለኛ መፍትሔ ማግኘት፣ ሥራን በሚገባ ማከፋፈልና ስነ ስርዓትን በደንብ ማስከበር ያስፈልጋል:: በተጨማሪ፣ የቀዩ ሠራዊት ቁሳቁሳዊ የኑሮ ሁኔታ ይሻሻል ዘንድ፣ የሠራዊቱን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ አስፈላጊውን ዘዴ መተለም፣ ሠራዊቱ ያርፍና ያገግም ዘንድ ባሉት ሁኔታዎች በሙሉ መጠቀም::

ንቃትን ከፍ ለማድረግ በምንሰማራበት ጊዜ፣ በሕብረተሰብ አንፃር ሲታይ ግለኝነት፣ ፖርቲው ውስጥ ሰርጎ የገባ የንዑስ ከበርቴና የከበርቴ ርዕዮተ ዓለም ነፀብራቅ መሆኑን ማስረዳት አለብን::

## የሽፍታነት አዝማሚያ

በቀይ ሠራዊት ውስጥ መደበ ቢስ /ኒሂሊስቱ ኤለመንትስ/ ግለሰቦች በመኖራቸውና በሃገሪቱ ውስጥ በብዛት ተመሳሳይ ግለሰቦች በመኖራቸው፣ በተለይ በደቡብ ክፍለ ሃገሮች ውስጥ በፖለቲካ አንጻር የሽፍታነት አዝማሚያ በቀይ ሠራዊቱ ውስጥ ሰፍኖ ነበር::

የዚህ አዝማሚያ ምልክቶች::

1ኛ/ መመርኮዣ ሰፈራቻና ሕዝባዊ ሰልጣን በትግል በመመሥረት የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት መታገል ቀርቶ፣ በአርበኞቻቸን አንቀበቃሉ ብቻ የፖለቲካ ድጋፍን ለማግኘት የመጣጣር አዝማሚያ፣

2ኛ/ ቀይ ሠራዊቱን ለማዳበር፣ ያከባቢ ጦሮችን በብዛት በማደም ከዝም ወደ መሠረታዊ ጦር ኃይል የማገበበበ ዝንባሌ፣

3ኛ/ በሰፊው ሕዝብ ጎን ተሰልፍ የከረረ ጦርነቶችን ማካሄዱ የመናቀና፣ በተቻለ ፍጥነት በትላልቅ ከተሞች ደርሶ እንደተፈለገው የመዘረፍ ጉጉትና ናቸው::

እነዚህ የሽፍታነት ዝንባሌ ምልክቶች፣ ቀዩ ሠራዊት ሊያሟላ የሚገባቸውን ተግባሮች እንዳያሟላ የሚደናቀፉ እንቅፋት ይሆኑታል:: በቀዩ ሠራዊት የፓርቲው ድርጅቶች ውስጥ ይህን አዝማሚያ መንገር ለማውጣት ከፍተኛ የርዕዮት ዓለም ትግል ማካሄድ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው አሳማ የሚሆነውም ለዚሁ ነው:: በነ ሁ አንግ ቻዎና በነ ቺያንግ ጊዜ የነበረውን አይነት፣ ይህን የመሰለ አዝማሚያ አሁን ባለንበት ጊዜ ፍፁም ተቀባይነት ሊኖረው እንደማይችል መረዳት ያስፈልጋል::

ይህንን አዝማሚያ ለማጥፋት:—

1. የሽፍታነት አዝማሚያን ለማጥፋት የማንቃቱን ተግባር ማጠናከር፣ በተሳሳቱ ዝንባሌዎች ላይ ሂስ ማቅረብ፣

2. በቀዩ ሠራዊት ውስጥ፣ በተማረኩ ወታደሮችና በቅርብ በተመለመሉት ዘንድ የማንቃቱን ተግባር ማጠናከርና ብሎም የውስለትና መንፈስን መደምሰስ፣

3. በቀይ ሠራዊቱ ውስጥ ታጋይና የትግል ልምዱ ያላቸው ወዛደሮችን አርሶ አደሮች ማስገባት፣ ብሎም የቀይ ሠራዊቱን ይዘት መቀየር፣



4. በትግሉ በሚሰቃዩ ወዛደሮችና አርሶ አደሮች አዳዲስ የጦር ክፍሎች ማቋቋም::

## የፑቺዝም ተቀጽላ

ፑቺዝምን ከቀዩ ሠራዊት የፓርቲው ድርጅቶች ውስጥ በበቂ ባይሆን ታግለናል:: ሰለዚህ አሁንም በቀዩ ሠራዊታችን ውስጥ የፑቺዝም ዝንባሌዎች ይገኛሉ:: ዝንባሌዎቹም በሚከተሉት ሁኔታዎች ይንፀባረቃሉ፣

1. በሚታዩና ነባራዊ ሁኔታዎችን በሚገባ በንመረምር ጭፍን እርምጃዎችን በመውሰዱ፣

2. በከተሞች የምንከተለውን ፖለቲካ ባልተሟላና በሚያወላውል አኳኋን ሰላካሄዱን፣

3. በተለይ ደግሞ በተመታንበት ጊዜ የወታደራዊ ሥነ ሥርዓትን ችላ በማለት፣

4. አሁንም አንዳንዱ የሥራ ክፍሎች ቤት ማቃጠልን ሥራዬ ብለው በመያዛቸው፣

5. ከሃዲዎችን በመግደልና በሰውነት ላይ ጉዳት መጣል በመባሉ ፑቺስት አሰራሮች በመጠቀም፣

የፑቺዝምን ሕብረተሰባዊ መሠረቶች በበዝነውና በገጠር ከበርቴው ርዕዮት ዓለሞች ጋብቻ ውስጥ ልናገኘው ይገባል::

ፑቺዝምን ለማጥፋት

1. ፑቺዝምን በርዕዮት ዓለም ደረጃ መደምሰስ፣
2. ሕጎችን ደንቦችና የፖለቲካ እርምጃዎችን በመደንገግ ፑቺስት አሠራርን መቋቋም::

ማ ጠ ቃ ለ ያ

እንገዲህ ስለ ሕዝባዊ ጦር ነትና ስለ ሕዝባዊ ሠራዊት ትርጉም አጭር ጥናት ለማቀረብ ሞክረናል። የጽሑፉ ይዘት ቴዎረቲካል እንጂ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተያይዞ በአሁኑ ወቅት በዚህ ጥያቄ አከባቢ ለሚቀርቡት ጥያቄዎች ተጨባጭ መልስ የሚሰጥ አይደለም። ሆኖም ግን በጽሑፉ ከሰፈረት አስተሳሰቦች እንዲሁም ደግሞ የለቁ ለቁ አብዮቶች ታሪክ ባገራችን ዛሬ ለሚነሱት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያስችሉ መመሪያዎች ሰፍረዋል። እነዚህን መመሪያዎች ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር አያይዞ ተጨባጭ መልስ መስጠቱ ያገባብያን ኃላፊነት ይሆናል። በዚህ መጽሔት ያቀረብነው ጽሑፍ አላማው ይህ አለነበረም። ነገር ግን ለወደፊት በተለይ ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተያያዘ ጥናት መቅረብ ደኖርበታል እንላለን።

ለማንናውም በተጨማሪ ከአዲስ ፋና መጽሔት የተገኘ የኢትዮጵያን ሁኔታ በቅርብ የሚያትት ጽሑፍ አያይዘን አውጥተናል።



# ሕዝባዊ ጦርነትና የኢትዮጵያ አብዮት

ከበለጠ ኃይሉ

"በአሁኑ ዓለም አቀፍ ሁኔታ ደካማና ትንሽ የሆነች አገር እንኳ ፣ ብትተባበር ፣ በወዝአደሩ ትግል አመራር ሥር ብትቆም ፣ ለነፃነትና ለዲሞክራሲ በቆራጥነት ብትታገል ማንኛውንም ወራሪ በማያዳግም አኳኋን ለማሸነፍ ትችላለች"

ሆ.ቺ.ሚንህ

በከፊል ፊውዳልና በከፊል ቅኝ ኀብረተሰቦች ውስጥ የሚገኙት ጭቁን ሕዝቦች ጠላቶቻቸውን ደምስሰው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን ለመመሥረት በሚያደርጉት ተጋድሎ ሕዝባዊ ጦርነት የሚያቀዳጃቸው ድል መሠረታዊና ከፍተኛ የትግል መሣሪያ ነው ። በተለይም በቻይና ፣ በቬትናም ፣ በላኦስና በካምቦዲያ እንደታየው ፣ የነዚሁ አገሮች ጭቁን ሕዝቦች ጠንካራና ጨካኝ የሆኑትን በኢምፔሪያሊስቶች እስከ መጨረሻው ድረስ የተደገፉትን አድሃሪ መንግሥታት ለማንበርከክ የተጠቀሙበት መሣሪያና የተጎናጸፉበት ጎዳና ሕዝባዊ ጦርነት ነው ። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮት በማካሄድ ላይ በሚገኙበት ወቅት ከጠላቶቻቸው ጋር በሚያደርጉት ትንንቅ ውስጥ ሕዝባዊ ጦርነት ሊጫረው የሚችለውን ቦታ መመልከት ይጠቅማል ፣ ያሻልም ። በተለይ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶች የትግል ሥልቶቻቸውን ከመቼውም በበለጠ አጠናክረውና ወደ ከፍተኛ ደረጃ አሸጋግረው የኢትዮጵያን አብዮትና አንድነት በጦር መሣሪያ በሚፈታተኑበት ባሁኑ ወቅት ፣ የሕዝባዊ ጦርነት ጥያቄ ከፍተኛ ግምትና ትርጉም ሊሰጠው ይገባል ።

ወደኢትዮጵያ ከመምጣታችን በፊት የሕዝባዊ ጦርነትና ምንነቱን ማወቅ ስለሚያስፈልግ ፣ አስቀድመን ሕዝባዊ ጦርነት ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ እናንሣ ፣ ይህም በዚሁ አካባቢ ያለውን ውዥንብር ለማስወገድ ይጠቅማል ። ለምሳሌ አንዳንድ የሕዝባዊ ጦርነትን ሳይንሳዊ ምንነት ያልተረዱ ሰዎች ሕዝባዊ ጦርነት በደፈናው በሕዝብ የተደገፈ ጦርነት ይመስላቸዋል ። ሌሎች ደግሞ ከከተት ሠራዊት ጋር ያመሳስሉታል ፣ በግራ ቀደም የሎርቃንት በሽታ የተለከፉ የንዑስ ከበርቴ ድንፋዎች ደግሞ ሕዝባዊ ጦርነት እንዲሁ መሣሪያ ይዞ ጫካ መግባት ይመስላቸዋል ። እነዚህ ሁሉ ስህተተኛ ግምቶች ናቸው ።

ትክክለኛውን ሳይንሳዊ ትርጉሙን የተከተልን እንደሆነ ሕዝባዊ ጦርነት ማለት በኢምፔሪያሊስት ቀንበር ሥር የምትማቅቅ ከፊል ፊውዳል ፣ ከፊል ከበርቴ የሆነች ሀገር ውስጥ የሚገኙት የተጨቆኑ ሕዝቦች ለብሔራዊ አርነትና ለአብዮት በወዝአደሩ ፓርቲ አመራርና የማርክሲስት ሌኒንስት ወታደራዊ መርሆችን በመ

ከተል የሚያካሂዱት ጦርነት ነው ። በመሠረቱም በትጥቅ ረገድ በጣም ደካማ የሆኑት የሕዝብ ኃይሎች እስከአፍንጫው ድረስ የታጠቀውን አድሃሪ ጠላት በየደረጃው እያዳከሙት ፣ በአንፃሩም ራሳቸውን እያጠናከሩ ድልን የሚጎናጸፉበት መደበኛ ታክቲክ ነው ። ይህን የሰጠነውን ትርጉም በበለጠ ለማስረዳት እንደሚከተለው እንተነትነው ።

ሕዝባዊ ጦርነትን ሕዝባዊ ጦርነት የሚያሰኘው የፖለቲክ ይዘቱና ዓላማው እንደመሆኑ መጠን ፣ ግቡም ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮትን ለማካሄድ ስለሆነ ፣ የወዝአደሩ ፓርቲ ፖለቲካል መሪነት ያስፈልገዋል ። ምንም እንኳ በጠላትና በሕዝብ መካከል የሚካሄደው ትግል በመጨረሻ ደረጃ የሚወሰነው በጦር ሜዳው ቢሆንም ፣ የሀገሪቷንና የዓለምን ሁኔታ በማጤን ሰፊውን ሕዝብ ሊያሰልፍ ፣ ጠላትን ሊያዳክምና ሊከፋፍል የሚችል ትክክለኛ ፖለቲካ መሥመር መቀየስ የሚችል አመራር ያስፈልገዋል ። አለበለዚያ ግን (ማለትም ትክክለኛ አመራር ከሌለው) ፣ ሰፊውን ሕዝብ በወታደራዊ እንገር ከመሸነፍ የሚያድነው አንዳችም ነገር የለም ። አንድ ደካማ ሠራዊት በራሱ ጉልበት ለመጠናከርና ጠላትን ለማሸነፍ የሚችለው ፣ የሀገሪቷን የፖለቲካ የልብ ትርታ አበጥሮ ያወቀ ፣ የጠላትን ድክመቶችና ስህተቶች ተረድቶ በነዚሁ መጠቀምና እንዲሁም የሕዝቡን ትግል ማቀነባበር የሚችል ወዘተ ... አመራር ሲኖረው ብቻ ነው ። የቬየትናም ሕዝባዊ ሠራዊት መሪ የሆነው ጂያፕ "ሕዝባዊ ጦርነት ፤ ሕዝባዊ ጦር" በተሰኘው መጽሐፉ ስለዚሁ ሲናገር የሚከተለውን ይላል ፤

'በምን ምክንያት ነው ፤ ምንም እንኳ ለጋ ቢሆንም ፤ ሠራዊታችን በጣም አኩሪ ታሪክ ሊኖረው ፣ አስደናቂ ወታደራዊ ድርጊቶችን ሊፈጽምና ለሕዝባችን አብዮት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክት የቻለው ? ምክንያቱ በፓርቲያችን የሚመራ ሕዝባዊ ሠራዊት በመሆኑ ነው ። ይህ አመራር ለሠራዊታችን ድሎች በሙሉ ወሳኝ ምክንያት ነው ።

ሀ. ሕዝባዊ ጦርነት በወዝአደሩ ፓርቲ ይመራ እንጂ በመደብ ይዘቱ የገበሬው ትግል ነው ። ማለትም የገጠር አብዮትና ሕዝባዊ ጦርነቱ ጣምራ ሆነው የሚሄዱ ናቸው ፦ ሰፊውን ሕዝብ ፤ ማለትም ሰፊውን አርሶ አደር ፤ በሕዝባዊ ጦርነት ውስጥ ለማሳተፍ የሚቻለው ትግሉ የአፈር ገፊውን መደብ ጥቅም መጠበቅ ከቻለ ብቻ ነው ። ገበሬውን ያላሳተፈ "ሕዝባዊ ጦርነት" የጥቂት ንዑስ ከበርቴ ደንፊዎች ውር ውር ከመሆን አያድንም ። እንዲያውም በገበሬው ራሱ መደምሰሱ አይቀርለትም ። የወዝአደሩ የፖለቲካ አመራር የሚያስፈልግበትም አንዱ ምክንያት ይኸው የወዝ አደሩንና የአርሶ አደሩን ኅብረት በመመሥረት ሰፊውን ጭቁን ገበሬ በአብዮቱ በጦርነቱ ለማሳተፍ ነው ።

ለ. ሕዝባዊ ጦርነት የሚመራው በማርክሲስት ወታደራዊ መርሆች ነው ። እርግጥ ማናቸውም ዘመናዊ ጦርነት የሚመራባቸውና የሚተዳደርባቸው አጠቃላይ የሆኑ ሕግጋት አሉት ። ሆኖም አንድ በትጥቅ ያልደረጀ ለአርነቱ የሚታገል ጭቁን ሕዝብ ወታደራዊ ድሎችን ሊጎናጸፍ የሚችልበት ጎዳና ዘመናዊ ቋሚ ሠራዊቶች ከሚመሩበት ስትራቴጂና ታክቲክ ለየት ያለ መሆን ይኖርበታል ። ማለትም በሕዝብና በጠላት መሀል ካለው የኃይል አሰላለፍና ሚዛን ተነስቶ ፤ ይህንኑ ከሕዝቡ ንቃት ፤ ድርጅትና ትጥቅ ደረጃ ፤ ከሀገሪቷ የኢኮኖሚ ሁኔታና የጂኦግራፊ አቀማመጥ እንዲሁም ከዓለም የፖለቲካ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ለሕዝቡ ትግል የሚበጅ ወታደራዊ ታክቲክና ስትራቴጂ መተለም ይኖርበታል ።



በተለይም ወደ ድል ለማምራት ሰፊው በሚራመድባቸው የትግል ደረጃዎች ፤ ማለትም ከተከላካይነት ወደ አቻነት በኋላ ወደ አጥቂነት (Stages of contention - equilibrium-offensive) በሚሸጋገርበት ጊዜ ከነዚሁ የትግል ደረጃዎች ጋር የሚመጣጠኑ ወታደራዊ ታክቲኮችና ስትራቴጂዎች ያሹታል ። ከታሪክ እንደምንማረውም የተሳኩት ሕዝቦች ብዙውን ጊዜ ትግላቸውን በሽምቅ ተዋጊነት ጀምረው ረዥምና ውስብስብ በሆነ ትግል በየደረጃው ወደ ዘመናዊ ተንቀሳቃሽ ጦርነት (Mobile Warfare) በማሸጋገር ነው ጠላትን ለማሸነፍ የቻሉት ።

ሐ. ሕዝባዊ ጦርነት የሚመራው በመጀመሪያ ደረጃ ራስን መቻል በሚለው መርሆ ነው ። የሕዝባዊ ጦርነት አንዱ ዓላማ ሀገሪቷን ከኢምፔሪያሊስት ተጽእኖ ነፃ ለማውጣትና የሀገሪቷን ሕልውና ለማስከበር እንደመሆኑ መጠን ፤ ሰፊው ታጋይ ሕዝብ በዚሁ ትግሉ የተቻለውን ያህል በራሱ ኃይል በመተማመን ራስን መቻል በሚለው መርሆ ለመተዳደር ይታገላል ። እንደሁኔታው አስገዳጅነት የወዳጅ ኃይሎች እርዳታ ካስፈለገው ፤ ብሔራዊ ነፃነቱንና ክብሩን በማይፃረር አኳኋን ዕርዳታዎችን ሊቀበል ይችላል ። የቬየትናም ጓዶቻችን በጦርነቱ ጊዜ በርካታ ከሁሉ አቅጣጫዎች የሞራልና የማቴሪያል ዕርዳታ ቢያገኙም ፤ የነበራቸው ብሩህ አብዮታዊ አመራር ተከትሎት በነበረው ረቂቅ ዲፕሎማቲክና የፖለቲካ መስመር አማካኝነት የሀገራቸውን ነፃነት ላለማስደፈር በቅተዋል ፤ እኛም ሆንን ሌሎች ታጋይ ሕዝቦች ከነርሱ መማር ይኖርብናል ።

የሕዝባዊ ጦርነት መሠረታዊ ነጥቦች እነሆ ከላይ የገለጽኳቸው ሲሆኑ ፣ የሚከተለው ጥያቄ እንግዲህ ሕዝባዊ ጦርነት በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ ቦታ አለው ወይ ? የሚለው ነው ። አንዳንድ የአብዮቱ ደጋፊዎች የኢትዮጵያን አብዮት ልዩ ሂደት ፣ የተገኙት ድሎች የዛን ያህል አስቸጋሪ ባልሆነ አኳኋን መገኘታቸውን ፣ በሀገሪቷ ውስጥ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ለተራማጆች አመቺ መሆኑን ፣ የፖለቲካ ሥልጣን እስካሁን ድረስ ከአብዮቱ ወገን በቆመ ደርግ መገኘቱን ፣ የመሬት ጥያቄ ከሞላ ጎደል በመፈታት ላይ መሆኑን ወዘተ...በማየት ሕዝባዊ ጦርነት ካሁን ወዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ ቦታ እንደሌለው አድርገው ይናገራሉ ። በእኔ ግምት ይህ አስተሳሰብ ፍጹም ስህተተኛ ነው ። ሁለት ምክንያቶች አሉኝ ። አንደኛ ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ግቡን እስካልመታ ድረስ በማናቸውም ጊዜ ተቀልብሶና የሕዝቡም የትግል ደረጃ ወደኋላ ተወርውሮ እንደገና 'ሀ . ሁ' ብለን መነሣት ሊያስፈልገን እንደሚችል መረሳት የለበትም ። ሁለተኛ እርግጥ እንደተባለው የኢትዮጵያ አብዮት ልዩ ሂደት እንዳለው ፣ የፖለቲካ ሁናቴው ለተራማጆች አመቺ እንደሆነ ፣ የፊት ለፊት ጠላቶቹ በቀላሉ ሊመቱ እንደቻሉ ወዘተ... የማይታበል ሐቅ ነው ። ነገር ግን ይህ የሕዝባዊ ጦርነትን አስፈላጊነት የሚሽር ሳይሆን ፤ በተለየ ሁኔታ መካሄድ እንዳለበትና የተለየ የአቀራረብ መልክ እንደሚያስፈልገው ነው የሚገልጸው ። ማለትም ለውጡ የይዘት ሳይሆን የመልክ ነው ። ላስረዳ ።

የፊት ለፊት ጠላቶቻችንን በሀገር ውስጥ ብንመታቸውም ፤ እነሆ ውጭ ተደራጅተው የኛን አብዮት ለማጥቃት በማሰፍሰፍ ላይ ይገኛሉ ፣ አቀራረባቸውን ቀይረዋል ማለት ነው ። በኢትዮጵያም ከአብዮቱ ፈጣን ሂደት የተነሣ ፤ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጠላቶቻቸውን ለመውጋት እርግጥ ወደ ሽምቅ ተዋጊነት መሠማራት አያስፈልጋቸውም ። ባለው አመቺ ሁኔታ ተጠቅመው ራሳቸውን በከፍተኛና በዘመናዊ የጦር ስልት አደራጅተው ጠላቶቻቸውን ማጥቃት ይችላሉ ፤ ይኖርባቸዋልም ። ይህ የሚ

ያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባዊ ጦርነት እንደማያስፈልግ ሳይሆን ፣ በተለየ አኳኋን በከፍተኛ ደረጃ መካሄድ እንዳለበት ነው ።

እንግዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝባዊ ጦርነት ያስፈልጋል የሚለውን አባባል ከተቀበልን ይህ ጦርነት ሊመራና ሊካሄድ የሚችልበትን ሁኔታ ለመወሰን ፣ በጠላቶችም ሆነ በሕዝቡ በኩል ያለውን የጦር ሁኔታ ፣ ብቃትና ስልት ማጥናትና አበጥሮ ማወቅ አስፈላጊ ነው ። በዚሁ አኳያ ይህንኑ ለማስቻል አስቀድመን በጠላቶቻችን በኩል ያለውን ሁኔታ እንመልከት ።

## 1. ኤርትራ

በኤርትራ ክፍለ ሀገር ኢ.ኤል.ኤፍ. እና ፒ.ኤል.ኤፍ የተባሉ ሁለት የተገንጣዮች ድርጅቶች ሲገኙ ፣ በለንደን የሚገኘው የስትራቴጂክ ጥናቶች ድርጅት (strategic studies) ከሚያወጣቸው መጽሔቶች ለመረዳት እንደሚቻለው ፣ ኢ.ኤል.ኤፍ. የተባለው ድርጅት በተዋጊዎችና በረዳት ተዋጊዎች ቁጥር ከፒ.ኤል.ኤፍ. ይበልጣል ። በዲሲፕሊንና በድርጅት ፒ.ኤል.ኤፍ. የተባለው ድርጅት ሲሻል ፣ ኢ.ኤል.ኤፍ. በዚህ አንፃር በጣም ወደኋላ የቀረ ነው ። ምንም እንኳ በተለያዩ ምክንያቶች ሁለቱ ድርጅቶች በርኩት ያለ ጊዜ እርስ በእርሳቸው የሚፋጁ ቢሆንም ፣ ሁለቱም በመሠረቱ አድሃሪ ድርጅቶች ናቸው ። በመሃከላቸው አንዳችም መሠረታዊ የፖለቲካል ልዩነት የለም ። ሁለቱም የኢትዮጵያን አብዮት በመቃወምና በውስጣቸው የሚገኙትን ተራማጅ ኃይሎች በመጨፍጨፍ አድሃሪነታቸውን በብቃት አሳይተዋል ። እስከተወሰነ ድረስ የኤርትራን ሕዝብ ለማወናበድ የበቁት ኃይለ ሥላሴ በኤርትራ ሕዝቦች ያካሂድ በነበረው ጭቆና ከዚያም ወዲያ በተፈጸሙት አንዳንድ ስህተቶች በመጠቀም ነው ። በወታደራዊ አንፃር ሁለቱን ድርጅቶች የተመለከትናቸው እንደሆነ ፡-

— ከአረብ አገሮች በሚጎርፍላቸው መሣሪያ ድጎና የታጠቁ ናቸው ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህም ከባድ መሣሪያ እንደሚጎርፍላቸው ይነገራል ።

— ምንም እንኳ አንዳንዶ ከኢትዮጵያ መለዮ ለባሽ መደበኛ ጦርነት ቢገጥሙም ፣ በዘመናዊ ጦር ስልት ስላልተደራጁ ፣ በዚህ እስካሁን ሊገፉበት አልቻሉም ። ማለትም የጦር ታክቲካቸው ከሽምቅ ተዋጊነት ወደ መደበኛ ጦርነት ፣ ከዚያም ተመልሶ ወደኋላ ወደ ሽምቅ ተዋጊነት ማፈግፈግ ወዘተ ...ነው ፤ ሁለቱን ታክቲኮች በማፈራረቅ ይጠቀሙባቸዋል ።

— በስንቅ ችግር ምክንያት ለረዥም ጊዜ ተዋጊዎቻቸውን ባንድ ቦታ ለማከማቸት ሆነ ረዘም ላለ ጊዜ ለማዝመት አይችሉም ። ምክንያቱም ሠራዊቶቻቸውን የሚቀልቡት የአካባቢውን ሕዝብ በመዝረፍ ስለሆነ ፣ ባንድ ቦታ ለብዙ ጊዜ ሊቆዩ አይችሉም ። ስለዚህም በየጊዜው ሠራዊታቸውን ለመበተን ፣ ለመሰብጣጠር ይገደዳሉ ። በዚህ በኩል በ1975 (UPPSALA/Sweden) የቀድሞው የኤርትራ ግምባር ተዋጊዎች አሁን ከኢትዮጵያ አብዮት ጋር የተሰለፉ ጓዶች ያወጡትን ዘገባ መመልከቱ ይጠቅማል ።

## 2. ሶማሊያ

ሶማሊያ ምንም እንኳ ከአያሌ ዓመታት አንስቶ ኢትዮጵያን ለመውጋት አቅሟ ከሚፈቅድላት በላይ የጦር ዝግጅት ብታደርግም እስካሁን ድረስ በቀጥታ ኢትዮጵያን በወታደሮቿ ለመድፈር አልቃጣችም ። ለጊዜውም የምትከተለው ታክቲክ ፡-

ሀ/ ከዚህ በፊት ተወናብደው ሶማሌ ገብተው የነበሩና ከብዙ ሥቃይ በኋላ ምህረት ጠይቀው የተመለሱት እንደሚናገሩት ከሆነ ሶማሊያ እስከ 40.000 ሰርጎ ገቦች አሰታጥቃ ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ዕቅድ እንዳላት ነው ። የዚሁ ዕቅድ ዓላማ ወደፊት ሶማሊያ በኢትዮጵያ ለምታካሂደው ማናቸውም ወረራ ሁናቴውን



ከማመቻቸትና የኢትዮጵያን ወታደሮች በሌላ አቅጣጫ ወጥሮ ለመያዝ ነው ፡ ሠርጎ ገቦቹን ለመመልመል የምትጠቀምበትም ታክቲክ ብሔረሰቦችን በማጋጨት ቢሆንም የኢትዮጵያ አብዮት የደቡቡን ሕዝብ ጥቅም በሚገባ እየተንከባከበና እንዲሁም የብሔረሰቦችን ችግር ለመፍታት ጉዳዩን እየጠረገ ስለሆነ ሶማሊያ በዚሁ አንፃር ግቧን ለመምታት የምትችል አይመስለኝም ፣ ቢሆንም የሠርጎ ገቦቹ ነገር በተወሰነ ጊዜ ሊናቅ የማይችል አደጋ መሆኑ አይቀርም ፡

ለ/ የጅቡቲን ነፃነት አድፍጣ ትጠባበቃለች ። ከተቻለ ጅቡቲን ጠቅላላ ቁጥጥሯ ሥር ለማስገባት ፣ ካልሆነም ከፈረንሣይና ከአድሃሪ የዓረብ አገሮች በመመሳጠር በጅቡቲ አሻንጉሊት የሆነ መንግሥት እንዲቋቋምላት ትጥራለች ። የኢትዮጵያ መንግሥት የጅቡቲ ነፃነትና ክብር እንዲደፈር የማይፈቅድ መሆኑንም ስለምታውቅ ፡ በዚሁ አንፃር ለጦርነት እየተዘጋጀች ነው ።

## 3. ኢ.ድ.ህ.

ኢ.ድ.ህ. የተሰኘው የከበለሉ መሳፍንት ድርጅት ፣ በወታደራዊም ሆነ በፖለቲካ ሒደው የአዲስ አበባው ደንቆሮ አድሃሪ እንደሚያወራው ሳይሆን ደካማ ድርጅት ነው ። ይህ በልፍስፍስ አድሃሪያን የሚመራው ፡ ወታደራዊ ሆነ ፖለቲካዊ ልምድ የሌለው ድርጅት እስካሁን ድረስ ከሚመጸወቱት አድሃሪ አረብ መንግሥታት መጫወቻና ኢትዮጵያን የሚያስፈራሩበት አሻንጉሊት ከመሆን አላለፈም ፡ ሊያልፍም አይችልም ። ምናልባት ወደፊት በተለይ በሰሜን በኩል የሕዝቡ ንቃት ባለበት የረገጠ እንደሆነ ኢ.ድ.ህ ፣ በዚሁ የንቃተ ሕሊና ወደኋላ መቅረት በመጠቀም ለተወሰነ ጊዜ ሊያንሠራራ ይችል ይሆናል ። ካሁኑ አፋጣኝ የሆነ ወታደራዊ እርምጃ ከተወሰደበትና በርሱም ሳቢያ በጐንደር የመሬት ድልድሉን ማከናወንና ሕዝቡን ማንቃትና ማደራጀት ከተቻለ ባጭር ጊዜ ውስጥ የኢ.ድ.ህ ምዕራፍ እንደሚዘጋ አያጠራጥርም ።

## 4. ሱዳንና ግብፅ

በፀረ ኮሚኒስት ቃልኪዳን የተሳሰሩት ሱዳንና ግብፅ በኢምፔሪያሊስቶች አቀነባባሪነት የኢትዮጵያን አብዮት ለማጥፋት ፡ ካልሆነም ለማዳከም ሲሉ በኢትዮጵያ ላይ ግልጽ የሆነ ወረራ ጀምረዋል ። ለሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብም እንደተነገረው የሱዳን ወታደሮች በሰሜንና በምዕራብ ኢትዮጵያ ጥሰው በመግባት አንዳንድ ከተሞችን ይዘዋል ። ይህ ወረራቸው ለጊዜው ባለበት ቢቆምም ፡ የሚከተሉት ዓላማዎች ሊኖሩት ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ ፡-

ሀ/ ደርግ አብዮቱን አቀዝቅዞ ከነርሱ ጋር እንዲደራደር ተጽእኖ ለማድረግ ፣ በአንፃሩም ማስጠንቀቂያ መስጠት ፡

ለ/ የኢትዮጵያን ወታደራዊ ኃይልና ብቃት ፣ እንዲሁም በሰሜን ያለውን የፖለቲካ ሁኔታ አመቺነት ለመፈተን ፡

ሐ/ ለኤርትራ ተገንጣይ ቡድኖች አመቺ የሆነ ወታደራዊ ሁናቴ ለመፍጠር ፡

በሱዳንና በግብፅ ኢትዮጵያ ላይ የተቃጣው ወረራ ፣ ምንም እንኳ ለጊዜው ባለበት ቢቆምና የተወሰነ ዓላማ ያለው ቢመስልም ፡ ፈጽሞ በቀላል ዐይን ለማየት አይቻልም ። ወረራውን ለማፋፋም የሚያስችላቸው የሰውና የገንዘብ ኃይል አላቸው ። ሳዳት ምን ቸገረው ፣ ሥራ ፈትቶ ቀለብ ከሚጠብቁት ግማሽ ሚሊዮን ወታደሮች ከፊሉን ለሳውዲ አረቢያና ለአሜሪካን ዶላር ሽጦ በኢትዮጵያ ላይ ሊያዘምታቸው ይችላል ። የባንግላዴሽም ታሪክ በኛው ሊደገም ይችላል ። ማለትም የውጭ ወታደሮች በኤርትራ ገብተው ከእናት ሀገሯ ሊገነጥሏት ይሞክሩ ይሆናል ።

የኢትዮጵያ አብዮት ፈሩን ሳይለቅ ወደፊት የቀጠለ እንደሆነ ፣ የኢትዮጵያን አብዮት ለመደምሰስ ቆርጠው የተነሡት ኢምፔሪያሊስቶችና የአካባቢው አድሃሪያን ከእንደዚህ ዓይነቱ ተግባር እንደማይመለሱ መታወቅ አለበት ። በተለይም ባለፈው ዓመት የኤርትራ

ን ጥያቄ የአረብ ወይም የዓለም አቀፍ ጥያቄ
ለማድረግ የተቃጡት ሙከራዎች በሙሉ ወደ
ዚሁ አቅጣጫ ያመለክታሉ ። ለማናቸውም ፣
ወጣም ወረደ ፣ ባሁኑ ወቅት ለኢትዮጵያ አብዮ
ትና ሕልውና ዋና ዋና ጠንቅ የሆኑት የሱዳንና
የግብፅ መሪዎች ናቸው ። በተቀዳሚም ደረጃ
ለነርሱን ወደመቋቋሙ ማተኮር አለብን ።

በጠላቶቻችን በኩል ያለው ሁኔታ እነሆ ላይ
እንደተዘረዘረው ሲሆን ፣ ወደኛው ስንመጣ ጠ
ላቶቻችንን በአንድ አፍታ ለማሸነፍ የሚያስች
ለን ወታደራዊና ኤኮኖሚያዊ ኃይል እንዳሌ
ለን በቀላሉ ለማየት እንችላለን ። ይህን ስል
የዛሬውን ሁኔታ በማየት ብቻ ሳይሆን ፣ ወደፊ
ት ጠላቶቻችን በደቡብና በሰሜን ፣ ማለትም በየ
አቅጣጫው ፣ በተጠናከረ አኳኋን ያጠቁን እን
ደሆን ሊፈጠር የሚችለውን የተባባሰ ሁኔታ
በመመልከትም ነው ። እስካሁን ድረስ ጠላቶቻ
ችን በሙሉ ኃይላቸው እንዳልተነሡብን ፣ ረስ
ተን የጠላቶቻችንን ኃይል የናቅን እንደሆን ፣
ሌኒን እንደሚለው በጦር ስልት ውስጥ ከፍተኛ
የሆነውን ስህተት ከመፈጸም እንድንም ። በኛ
በኩል ወዳለው ወታደራዊ ሁኔታ እንመለስና ፣
የኢትዮጵያ ወታደሮች በየቦታው ተሠማር
ተው ፣ በየክፍለ ሀገሩ ተሰበጣጥረው የኢትዮጵ
ያን አብዮትና አንድነት ጠላቶች በመቋቋም
ላይ እንዳሉ እናያለን ። በሌላ በኩል ደግሞ በኢም
ፔሪያሊስትና በፊውዳል ብዝበዛ የተነሣ ድህነ
ትን የተቆራኘችው አገራችን በዐረብ ፔትሮ
ዶላርና በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም የተደገፈ
ወራሪን ሠራዊት ፣ ለረዥም ጊዜ በዘመናዊ
ወታደራዊ ደረጃ ለመቋቋም የሚያስችላት ኢኮ
ኖሚክ ብርታትና ብቃት የላትም ። እንግዲህ
ትልቁ ጥያቄ ፣ በርከት ባሉ ጠላቶች የተደፈረ
ችው ሀገራችን አብዮቷን እያራመደች ብሔ
ራዊ ነፃነቷንና ሕልውናዋን ለማስከበር ምን
ማድረግ አለባት ? ምን ለማድረግስ ትችላለች?
የሚለው ነው ።

ያለን አብዮታዊ አማራጭ አንድ ብቻ ነው ፣
ይኸውም ጠላቶቻችንን ለመቋቋም አብዮታዊ
ብሔራዊ ጦርነት ማካሄድ ነው ። በኢትዮጵያ
ሕዝብና አብዮት ሙሉ እምነት ኖሮን ፣ ሰፊው
ን የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገራችንን ነፃነትና ሕል
ውና ለማስከበር ለሚደረገው ትግል በመቀሰ
ቀስ ፣ የሕዝባችንን አብዮታዊ ኃይልና ግፊት
ሊበገር ወደማይችል የሀገር መከላከያ ጉልበት
ቀይረን ጠላቶቻችንን ለመደምሰስ ፣ በቀላሉ
የማይረሱትን ትምህርት ልንሠጣቸው እንች
ላለን ። ለዚህም የሕዝባችንና የሀገራችንን ጠቅ
ላላ ሞራልና ማቴሪያል ኃይል ብሔር ዐቀፍ
በሆነ ዝግጅት ማንቀሳቀስ ያስፈልጋል ።

ይህ ተግባር በተቀዳሚ ደረጃ ፖለቲካዊ
ነው ። ማለትም በሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝ
ብ መካከል በይዘቱ አብዮታዊ ፣ በመልኩ
ሀገር ወዳድ የሆነ ቅስቀሳ ማድረግ ፣ በ
ዚሁም መንፈስ ሕዝቡን ማደራጀትና ማ
ስታጠቅ ያስፈልጋል ። ሌኒን በዘመናዊ ጦ
ርነት የሚያሸንፈው "በሰፊው ሕዝብ ዘን
ድ ከፍተኛውን ሪዘርቭ ፣ አብዛኛውን የጉል
በት ምንጭና ከፍተኛውን ድጋፍ ያለው ወገን
ነው" ይላል ። እኛም ለምናካሂደው አብዮታዊ
ብሔራዊ ጦርነት ፣ የሕዝቡን ሙሉ ድጋፍ ለማ
ግኘት ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ቅስቀሳ ማድረ
ግ አለብን ። ይህ ቅስቀሳ ከላይ እንደጠቀስኩት
በይዘቱ አብዮታዊ ፣ በመልኩ ሀገር ወዳድ መሆ
ን አለበት ። በደፈናው ሀገር ወዳድ ቅስቀሳ
ማድረግ ብቻ አይበቃም ። ምክንያቱም እን
ደኛ ፣ የምናካሂደው ጦርነት የሀገራችንን ዳር
ድንበር ለመመልከት ብቻ አይደለም ፤ አብዮታ
ችንን ለመጠበቅና ለማራመድም ነው ። ሁለ
ተኛ ፣ አድሃሪያን እንደሆኑ ሀገራቸውን የከዱት
ዱሮውኑ ስለሆኑ ፣ በዚሁ አገር መከላከያ ዘመቻ
የሚሳተፈው በዛም አነሰ አብዮቱ የመጣለት
ጭቁኑ ሕዝብ እንደመሆኑ መጠን እርሱን በዚ
ሁ ትግል ለመሳብ ያለውን የትግል ወኔና የመስ
ዋዕትነት ፈቃደኝነቱን ድርብ ፣ ድርብርብ
ከፍ ለማድረግ ሀገር ወዳድና አብዮታዊ ቅስቀ
ሳን አጣምሮ ማካሄድ ያስፈልጋል ። በአንፃ
ሩም የሰፊውን ሕዝብ አብዮታዊነት ፣ የትግል
ፍላጐትና የመፍጠር ችሎታ (Creativity)



አፍና የያዘው የቢሮክራሲው ማነቆ ተደምስሶ
ሕዝቡ ...ነት ሊጥልበት በሚችል ፣ መልሶም
ሕዝቡን ለማንቀሳቀስና የሕዝቡን አብዮታዊ
ጉልበት አቅጣጫ ሊሰጠው በሚችል አዲስ አብ
ዮታዊ መዋቅርና የአሠራር ዘይቤ መተካት አለ
በት ። በዚሁ አቅጣጫ የመጀመሪያው እርምጃ
በሕዝቡ ዘንድ የተጠሉ እንዲሁም በአድሃሪነ
ታቸው እንከን የማይወጣላቸውን የአንዳንድ
ክፍለ ሀገራት ቢሮክራሲ ቁንጮችና እንዲሁም
በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ከፍተኛ የአመ
ራር ቦታ የያዙትን አድሃሪያን አንስቶ በተራማ
ጆች መተካቱ ሊሆን ይችላል ። በቢሮክራሲው
ላይ የማያወላውል እርምጃ ካልተወሰደ ፣ አጥ
ጋቢ በሆነ ሁኔታ ሕዝቡን ለመቀስቀስና ጥሩ
ውጤት ሊሰጥ የሚችል ሕዝባዊ የሆነ የመከላ
ከያ ኃይል ለማደራጀት እንደማይቻል መታወ
ቅ አለበት ። የቬትናም ጓዶቻችን ከፈረንሣይ
ኢምፔሪያሊዝምና ከአጼ ባኦ ዳይ የወረሱትን
የተግማማውን ቢሮክራሲ ደምስሰው አዲስ
በሆነ የአስተዳደር መዋቅር ባይተኩት ኖሮ ፣
ሠላሳ ዓመታት ሙሉ አኩሪ በሆነ አኳኋን ታግ
ለው ጠላቶቻቸውን ለማሳፈር ባልቻሉ ነበር ።
ከነርሱ መማር አለብን እላለሁኝ ።

የምናካሂደው ሕዝባዊ ጦርነት ፣ እውነተኛ
ሕዝባዊ ጦርነት እንዲሆንና እንዲሁም ጠላቶ
ቻችንን በማያወላውል አኳኋን ለማሸነፍና ለመ
ደምሰስ የሚከተሉት ፣

ሀ. ፖለቲካዊ ፣
ለ. ወታደራዊና ፣
ሐ. ስትራቴጂክ ሁኔታዎች በተጨማሪ
እንዲሟሉ መታገል ያስፈልጋል ።

ሀ· መሟላት ያለበት ፖለቲካዊ ሁናቴ
ሀገራችንን ለመላከል የሚደረገው ሕዝባ
ዊ ወታደራዊ ዝግጅትና ትግል አብዮታዊ
በሆነ የፖለቲካል አመራር ሥር መዋል
አለበት ። የአንድ ትግል አመራር የሚወ
ሰነው በትግሉ ይዘት ነው ። ምንም እንኳ
አብዮታችንን ለመደምሰስ ከተነሡት ጠላ
ቶቻችን ጋር የሚዋጣልን በትግሉ ሜዳ
ቢሆንም ፣ የጠቡ መነሻና ይዘት ፖለቲካዊ
እንደመሆኑ መጠን ፣ በዚሁ አንፃር ትግላ
ችንን የሚመራና የሚያደራጅ አብዮታዊ
የሆነ የፖለቲካ አመራር ያስፈልገናል ፣
እርግጥ እንደ ቻይናና ቬትናም ትግላችንን
ሊመራልን የሚችል የወዝአደር ፓርቲ
የለንም ። ቢሆንም ካሉት ተራማጅ ድርጅ
ቶች ፣ (ለምሳሌ ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስ
ተዳደር ደርግ ፣ ከተራማጆች ኅብረት ፣ ከሕ
ዝብ ድርጅት ጉዳይ ጊዜያዊ ጽ/ቤትና ከመ
ለዮ ለባሽ ካድሬዎች) የተውጣጣ አብዮ
ታዊ አመራር በዚሁ በኩል የሚጠበቅበ
ትን ለማከናወን እንደሚችል የሚያጠራ
ጥር አይደለም ፤
ይህ አብዮታዊ አመራር የሚከተሉትን
መሠረታዊ ተግባሮች ሊያከናውን ይች
ላል ።

1/ ብሔራዊ አብዮታዊ ጦርነትን በሚመ
ለከተው ረገድ ፣ መከተል የሚገባንን
ፖለቲካዊ ፣ ወታደራዊና ዲፕሎማቲክ
መሥመር በተቀነባበረ አኳኋን መቀየ
ስና ማስፈጸም ።
2/ ብሔራዊ አብዮታዊ ጦርነቱ እንዲሳካ
የሚያስፈልገውን አብዮታዊ ቅስቀሳና
ዝግጅት በፖለቲካ ፣ ኤኮኖሚና ሶሺያል
አንፃር መምራትን ማስፈጸም ።
3/ ብሔራዊ አብዮታዊ ጦርነቱ የወዝ አደ
ሩን ፓርቲ መመሥረትና ነፃ ሕዝባዊት
ዲሞክራቲክ ሬፑብሊክ ኢትዮጵያን
መቋቋም እንዲያረጋግጥ ከፍተኛ ጥን
ቃቄ የተመላበት ትግል ማድረግ ።

የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በሁኔታው
አሳሳቢነትና በተጣለበት ከባድ ኃላፊነት ማካሄ
ድ የሚኖርብን ብሔራዊ አብዮታዊ ጦርነት የተ
ሳካ ውጤት አግኝቶ በአብዮታችን ፣ የሀገራችን
ሕልውናና አንድነት ይጠበቅ ዘንድ ፣ ያለንበት
ሁኔታ እንደሚጠይቀው (ማንም ሐቀኛ አብዮ
ታዊ ደግሞ ሁልጊዜ አብዮታዊ ሁኔታ የሚጠበ
ቅበትን ግዴታ ያለማወላወል ለመፈጸም ዝግጁ
ነው) የሚደረገው ዘመቻ በየደረጃው አብዮታ
ዊ አመራር ማግኘቱን ማረጋገጥ ይኖርበታል ።

## ለ. መሟላት የሚገባቸው ወታደራዊ ሁኔታዎች ፡

1/ <u>በመደበኛው ሠራዊት በኩል ፤</u> ያለውን መደበኛ ሠራዊት ከመቼውም በበለጠ ማጠናከር ፤ በተሻሉ መሣሪያዎች ማስታጠቅና ፤ የውትድርናውን ችሎታ ከፍ ማድረግ ያስፈልጋል ። በኃይለ ሥላሴ ጊዜ በአምቻ ጋብቻ ተሹመው ከፍተኛ የአመራር ቦታ የያዙትን እንዲሁም የወጣላቸው አድኃሪ መኰንኖችን አንስቶ በቦታቸው ችሎታቸውን በገቢር ያስመሰከሩና አብዮታዊ የሆኑ መኰንኖችን መሾም ያስፈልጋል ። ባጠቃላዩም የመኰንኖችን ወታደራዊና ርዕዮተ ዓለማዊ የዕውቀት ደረጃ ያለማቋረጥ ማሻሻልና ከፍ ማድረግ ያሻል፡ የውጭ ወራሪዎችም ኢትዮጵያን በሚያጠቁበት ወቅት ይበልጡኑ የሚተማመኑት ባሏቸው <u>ከባድ መሣሪያዎች እንደመሆኑ መጠን</u> ፤ በዚሁ አንፃር የሠራዊታችን ከባድ መሣሪያዎችን ፡ ለምሳሌ ታንኮችን ፡ መድፎች ፤ ሮኬቶች ወዘተ ... ጥራትና መጠን በከፍተኛ ደረጃ ማጠናከር ያስፈልገናል ፤ <u>የአየርና የባህር ኃይሎቻችንም</u> (በቅርቡ የተደረገው የግብፅ ባህርና አየረ ኃይል ወታደራዊ ልምምድ እንዳሳየው) በሚካሄደው የሀገር መከላከል ጦርነት ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወቱ በአፋጣኝ ደረጃ ጥራታቸውን ጠብቀው የሚጠናከሩበትን መንገድ መሻት ያስፈልጋል፤

2/ <u>ብሔራዊ አብዮታዊ ሠራዊት ስለማቋቋሙ ጉዳይ</u> ፤ የኢትዮጵያ መደበኛ ሠራዊት ብቻውን የከበቡንን ጠላቶች ሊቋቋማቸው እንደማይችል ሁሉ ፤ ጐኑ ተሰልፎ አብሮት ሊዋጋ የሚችል በዘመናዊ ጦር ሥልት የተደራጀ ከሕዝብ የተውጣጣ ሠራዊት በአስቸኳይ ማቋቋም ያስፈልጋል ፤ ይህ መቋቋም ያስፈልገዋል የምለው ሠራዊት ፤ በአቋሙ በድርጅቱና በትጥቁ ከመደበኛው ሠራዊት ጋር አንድ ሲሆን ፤ የሚለየው በሚከተሉት ሁለት ነጥቦች ብቻ ነው፡

— በብሔራዊው አብዮታዊ ሠራዊት የሚገለገሉት ታጋዮች በደሞዝ ተቀጥረው፣ ማለትም በአበል ሳይሆን በበጐ ፈቃደኝነት ነው ፤

— በብሔራዊው ሠራዊት ከዕንሱ ጀምሮ የሚደራጀው በፖለቲካዊና በአብዮታዊ መንፈስ ነው ።

የብሔራዊ አብዮታዊ ሠራዊት አስፈላጊነትን ሚያዝያ ወር በወጣው የአዲስ ፋና እትም ጓድ በርታ በለው በሚገባ ስላስረዳው አልደግመውም ። ዋናው ነገር ያው በመጠንም ሆነ በጥራት በዘመናዊ ጦር ስልት የተደራጀ ሠራዊት አስልፈን ወደ አጥቂነት ለመሸጋገር እንዲያስችለን ነው ።

እርግጥ ብሔራዊ አብዮታዊ ሠራዊት በቀላሉ ሊቋቋም የሚችል ነገር አይደለም ። ብዙ ወጭንና ድካምን ይጠይቃል ። ወታደሮቹን ሆነ መኰንኖችን ለማሠልጠንም ጊዜ ይፈጃል ። ነገር ግን ሌላ አማራጭ መንገድ ስለሌለን ፤ በዚሁ ተግተን ይህንኑ የተቻለውን ያህል አፋጣኝ በሆነ መንገድ ማገባደድ ይኖርብናል ።

3/ <u>ሕዝባዊ ሠራዊት</u> ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ ግማሽ ሚልዮን አባላት ገደማ ያለው ሕዝባዊ ሠራዊት እንዳለ ይነገራል ። ይህ በውነቱ ቀላል ቁጥር ባይሆንም ፤ ሕዝባዊ ሠራዊቱ በአመራር በድርጅትና በትጥቅ ረገድ ካሉት አያሌ ድካሞች የተነሣ ፤ በኅብረተሰቡ ውስጥ ከቁጥሩ ጋር የሚመጣጠን ወታደራዊና ፖለቲካዊ ክብደት የለውም ። እነዚሁ ጉድለቶች በአፋጣኝ መወገድ አለባቸው ። በሚከተሉትም መንገድ የሚቻል ይመስለኛል ።

— በአንፃሩ የጠበቀ ፤ የተለያዩትን የሕዝብ ሠራዊት አካሎችን የሚያቀላልፍ ድርጅታዊ ሰንሰለትና ይበልጥ የተጠናከረ ማዕከላዊ አዛዥ ቢሮ ማቋቋም ፤



— በወታደሩ እንደሚደረገው በየአንዳንዱ የሕዝብ ሠራዊት አካል ፖለቲካዊ ካድሬዎች መመደብ ፤ በአጠቃላይ የፖለቲካ ካድሬዎች መዋቅር ለሕዝባዊው ሠራዊት መመሥረት ፤

— በተቻለ መጠን የሕዝባዊውን ሠራዊት የትጥቅ ደረጃ ማሻሻል ፤

ሕዝባዊ ሠራዊት ከመደበኛው ሠራዊት ጋር ሲነፃፀር በወታደራዊ ብቃቱ አነስተኛ መሆኑ ባይቀርለትምና ፤ በአካባቢው ቢወሰንም ፤ በንቀት ልንመለከተው የምንችል ኃይል አይደለም ። እንደዚህ ያለው አመለካከት ከባድ ስህተት ይሆንብናል ። ሕዝባዊው ሠራዊት

1/ የመደበኛው ሆነ የብሔራዊ አብዮታዊ ሠራዊቱን የተጓደለውን የሰው ኃይል የምንተካበት ምንጭ በመሆን ፤

2/ የአካባቢውን ፀጥታና ምርት በመጠበቅ ፤

3/ ካስፈለገም በሽምቅ ተዋጊነት በመሠማራት ለአብዮቱ ከፍተኛ አስተዋፅዖ የሚያበረክት ኃይል ነው ።

## ሐ. መሟላት ያለባቸው ስትራቴጂክ ሁኔታዎች ፤

1/ <u>በተለይ በሰሜን ክፍለ ሀገራት ሕዝቡ አብዮቱን እንዲደግፍ ማድረግ</u> ። በጐንደርና በኤርትራ ክፍላተ ሀገር የሚገኘው ጭቁን ሕዝብ በአድኃሪያን ክንቱ ስብከት ተወናብዶ አብዮቱን የተቃወመ እንደሆነ ፤ በአንፃሩ በዚሁ አካባቢ የኢትዮጵያ መንግሥት የሚወስዳቸው ማናቸውም ወታደራዊ እርምጃዎች የበለጠ ችግር እንደሚገጥማቸውና ለጠላትም አመቺ ሁኔታ እንደሚሰፍን ሳይታለም የተፈታ ነው ። በነዚሁ ክፍላተ ሀገ.. በጐንደርና በአንዳንድ ቦታዎች በተፈጠረው ችግር በቀጥታ በጭቁኑ ሕዝብ መካከል ፖለቲካዊ ቅስቀሳ ለማድረግ ባይቻልም ፤ ከሚወሰዱት ወታደራዊ እርምጃዎች ጋር አብሮ መሄድ አለበት ። ማለትም ሽፍቶቹ ከሚባረሩባቸው አካባቢ ያኔውኑ የፖለቲካ ቅስቀሳ ማድረግና የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም መንከባከብ ያስፈልጋል ። ለምሳሌ በጐንደር ክፍለ ሀገር አድኃሪያን ሰፊውን ሕዝብ በማወናበድና በማስፈራራት የመሬቱ ድልድል እንዳይከናወን ባገዱበት አካባቢ በነዚሁ አድኃሪያን ላይ የማያወላውል ወታደራዊ እርምጃ ወስዶ ፤ ለሰፊው ጭቁን ሕዝብ መሬት ከታደለ ፤ በርሱ መሀል ሰፊ የፖለቲካ ቅስቀሳ ከተደረገ ሰፊውን ሕዝብ ከአድኃሪያን ተጽዕኖ ፈልቅቆ በማውጣት ከአብዮቱ ጐን ማሰለፍ ይቻላል ። በአፋር ብሔረሰብ ምሳሌነትም እንዳየነው ፤ በኤርትራ ክፍለ ሀገር እንደዚሁ ሊደረግ የማይቻልበት አንዳችም ምክንያት የለም ።

2/ <u>"ሠራዊትህን አከማች አትሰበጣጥር" የሚለውን ወታደራዊ መርሆ በመከተል</u> ፤ ኢትዮጵያን የከበቧት ጠላቶች በሚያሰልፏቸው ወታደሮች በአጠቃላይ በስትራተጂ አንፃር የቁጥር ብልጫ ቢያሳዩም ፤ ኃይላችንን ሳንሰበጣጥር አከማችተን በተናጥል ብንወጋቸው ፤ በየአንዳንዱ ውጊያና ግጥሚያ የበላይነትን ለመቀዳጀት እንችላለን ። አንድ ሰው አምስት ጣቶች አሉኝ ብሎ አምስት የተለያዩ ነገሮችን ባንድ ላይ ሊይዝ አይችልም ። አንዱንም ሳይዝ ባዶ እጁን ይቀራል ። ተራ በተራ ግን ሁሉንም ሊያስገባቸው ይችላል ፤ ሁለተኛው ምንም እንኳ የምናካሂደው ብሔራዊ አብዮታዊ ጦርነት በመጀመሪያ ደረጃ የተከላካይነት ጠባይ ቢኖረውም ፤ ወራሪ ኃይሎቹን ለመደምሰስ በአፋጣኝ ወደ አጥቂነት መሸጋገር ስለሚያስፈልግ በዚሁ አንፃር በግድ ወታደሮቻችንን መሰብሰብና ማከማቸት ይኖርብናል ። በኛና በጠላቶቻችን መሃል ያለው የኃይል ሚዛን ወደኛው እንዲያዘምም የሚያገለግለን ፤ እኛ ከተከላካይነት ወደ አጥቂነት ፤ እነርሱ ከአጥቂነት ወደ ተከላካይነት እንድንሸጋገር የሚያደርግ መደበኛ ወታደራዊ ታክቲክ ነው ። እርግጥ ይህ ወታደራዊ ታክቲክ

እንደማናቸውም ታክቲክ በደረቁ የምንከተለው ሳይሆን ከየሁናቴው ጋር የምናገናዝበው ነው ።

3/ ጠላትን መከፋፈልና ማዳከም ፣ ጠላቶቻችን በአንድ ላይ እንዳይነሡብን ለማድረግ የሚዘምትብንንም ሠራዊት በምናደርጋቸው ወታደራዊ እንቅስቃሴቶዎች መከፋፈል ፣ ለአብዮታችን ፋታ የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ጠላቶቻችንን በቀላሉ እንድንደመስሳቸው ያስችለናል ። የራሳችንን ኃይል ጠብቀን ፣ እንደሁኔታው የጠላቶቻችንን አቅጣጫ መከፋፈልና እነርሱን ማዳከም የሚያዋጣንና ለኛ የሚበጅ ታክቲክ ነው ። በኢትዮጵያችን ሁኔታ ጠላቶቻችንን በዲፕሎማሲ ፣ በፖለቲካ ፣ በጦር ሜዳ ፣ በጂኦግራፊ አቀማመጣችን ወዘተ... ሁሉ ልንከፋፍላቸው ስለምንችል ፣ በነዚሁ ሁሉ መጠቀም የምንችልበትን ጥበብ እርቅቀን ማወቅ ይኖርብናል ።

4/ የጠላትን ነጥቦች ማወቅና ጠላት ስህተቶችን እንዲፈጽም ማድረግ ፣ የዚህ አስፈላጊነት በጣም ግልጽ ስለሆነ ብዙም መናገር አያስፈልገውም ። በተጨባጭ የአካባቢውን ሁኔታ ከተመለከትን በተለይ ኒሜሪ ልንገለገልባቸውና እርሱን ልናንበረክከበት የሚያስችሉን አያሌ ድካሞች አሉት ። በፖለቲካም መድረክ ሆነ በትርቡ ኢትዮጵያን ለመውረር በቃጣበት ጊዜ የሠራቸው ወታደራዊ ስህተቶች አሉ ፣ በነዚሁ ስህተቶች መጠቀም በበለጠም ስህተት እንዲሠራ ማድረግ ለትግላችን አመቺ የሆነ ሁናቴ ይፈጥራል ።

ለማጠቃለል ያህል ፣ እላይ የተዘረዘሩት የፖለቲካ ፣ ወታደራዊና ስትራቴጂክ ሁኔታዎች እንዲሟሉ ያልተቆጠበ ጥረት ከደረግን ፣ ለብሔራዊ ፍትህና ለአብዮታችን ወደፊት ግፊት የምናካሂደው ሕዝባዊ ጦርነት ድልን እንደሚቀዳጅ አያጠራጥርም ። የውጭና የውስጥ ጠላቶቻችንንም ደምስሰን በአዲሱ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ጐዳና የምትንዝም ነፃ ፣ የበለጸገች ጠንካራ ኢትዮጵያንም ለመመሥረት እንበቃለን ።

ለማሸነፍም ሆነ ለመሸነፍ ሁሉም የሚወሰነው የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚያካሂዷቸው ትግሎች ፣ በሚከተሏቸው ታክቲኮችና ስትራቴጂዎች ነው ። ከዚሁ ጋር በማያያዝ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ድልን እንዲጎናጸፉ ለማድረግ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበትና የሚወስዳቸውም ማናቸውም እርምጃዎች በዚህም በኩል ሆነ በዚያ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በሚያካሂዱት የሀገር መከላከያ አብዮታዊ ጦርነትና ታሪካዊ ጥረት ተፅእኖዋቸውን ማስማታቸው እንደማይቀር መታወቅ አለበት ። በተራማጆች ኅብረት ውስጥ ባሉ ድርጅቶች መሃል ስላለው ቅራኔ ይህ ቅራኔ በማርክሳዊ ሌኒናዊ መርህ መሠረት ሂስና ግለ - ሂስ በመጠቀም ዲሞክራሲያዊ ክርክር በማድረግ ሊቻቻል ይችላል ። በተራማጆች ኅብረትና በንዑስ ከበርቴው ሠፈር ያለውም ቅራኔ የንዑስ ከበርቴውን ሠፈር ይበልጡን አረጋግቶ ወደ አብዮቱ ሠፈር ለማቀላቀል ትግል ከተደረገ ይህም ቅራኔ እንዲሁ የሚቻቻል ነው ። በተረፈ በተራማጆች ኅብረትና በአገር ወዳዱ መሃል ያለው ቅራኔ ጨርሶ የማይናቅ ስለሆነ የተራማጆች ኅብረት በብሔራዊ ነጻነት ጥያቄ ላይ የሚኖረው አቋምና የቅስቀሳ ዘዴ አገር ወዳዱን የአብዮቱ አጋር አድርጎ በከፍተኛ ደረጃ ሊያሰልፈው ይችላል ። ሊቻቻሉ የሚችሉትን እነኚህን ውስጣዊ ቅራኔዎቻችንን አቻችለን ፣ በተቀዳሚ ደረጃ የሀገራችንንና የአብዮታችንን ጥቅም ለማስከበር ከታገልን ፣ የሚጠበቅብንንም ብሔራዊና አብዮታዊ ግዴታዎች ለመፈጸም ዝግጁ ከሆን ጠላቶቻችንን ከማሸነፍ የሚያግደን አንዳችም ነገር የለም ። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትም ተራማጅ ድርጅቶች ትልቅም ሆኑ ትንሽ ሁሉ ለዚሁ ለተቀደሰ ዓላማ መታገል አለባቸው ፣ ጽሑፉን ከመደምደሚ በፊት ግን ሕዝባዊ ጦርነት በምናካሂድበት ፣ ይህንኑ ሕዝባዊ ጥረት ሊያሰናክሉ የሚችሉትንና ከነርሱ መጠንቀቅ ያለብንን ስህተቶች በአጭር በአጭሩ ለመጠቆም ፈልጊአለሁ ። በእኔ ግምት ለዚሁ ታሪካዊ እቅዳችን ጠንቅ ሊሆኑ የሚችሉት የሚከተሉት የተሳሳቱ ግምቶች ናቸው ።



1. ቢሮክራሲው ሕዝባዊ ጦርነትን ሊመራ ይችላል የሚለው ግምት ፣

ይህ ግምት ፍጹም ስህተተኛ ከመሆኑም በተር፡ ከጥቂት ጊዜ ጀምሮ በአብዮቱ አፋጣኝ ሂደት የተደናገጡ ኃይሎች እንደመጨረሻው አስተማማኛቸው ቢሮክራሲውን በመቆጣጠር ለርሱ ጥብቅና በመቆም ከሚሰነዝሯቸው አድርባይ አስተሳሰቦች ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው ። የሕዝባዊ ጦርነት አመራር በተራማጆች ሥር መዋል እንዳለበት ከፍ ብለን ስላሳየን እዚህ እንደግመውም ። አንባቢያን መልሰው እንዲያዩት እንጋብዛለን ። ለማናቸውም እነዚሁ ኃይሎች የሚያቀርቧቸውን አድርባይ ፣ በእውነትም አስቂኝ ምክንያቶች እንመልከት ። እነዚሁ ኃይሎች የሚያቀርቡት አንደኛው ግምት ቢሮክራሲው ተራማጅ ነው የተሰኘውን ነው ። ይህ አባባል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ዲሞክራቲክ አብዮት ፕሮግራም ያዘትን የሚፃረር ብቻ ሳይሆን ፣ እስካሁን ድረስ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በዚሁ አንፃር ይከተል የነበረውን ፖለቲካ ፍጹም የሚቃረን ነው ። ለሥልጣን የቋመጡ አንዳንድ ቢሮክራቶች እድሜያቸውን ለማስረዘም ቢሮክራሲው ተራማጅ ነው ይበሉ እንጂ ፣ ሰፊው ሕዝብ ቢሮክራሲውን የሚያውቀው በአድሃሪነቱ ነው ። እነዚሁ ኃይሎች ከቢሮክራሲው ጋር አብሮ መሄድን ለመደገፍ የሚያቀርቡት ሁለተኛ ምክንያት ቢሮክራሲው እስካሁን ድረስ የጠቀመ ኃይል ነው ፣ ወደፊት ቀስ በቀስ እየተባለ ይቀየር ይሆናል እንጂ እንደብርጭቆ የሚሠበር ነገር አይደለም ይላሉ ፤ እርግጥ እንደብርጭቆ የሚሠበር ብርጭቆ ብቻ ነው ። ሁሉም ነገር እንደባህሪው የአሰባበር ዓይነት አለው፣ስለሆነም ቢሮክራሲው ይደምሰስ ሲባል እንደብርጭቆ ልትሠብሩት ትፈልጋላችሁ ብሎ መከራከሩ የሚያዋጣ አይደለም ። የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር ሌ·ተ·ና ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም በሚያዝያ 6 ቀን 1969 ዓ.ም. በአብዮት አደባባይ ለተሰበሰበው ሕዝብ የቢሮክራቲክ ካፒታሊዝም ደም እንደሚፈስ ለሰፊው ሕዝብ ቃል ገብተዋል ። ይህም ያው በቢሮክራሲው ላይ አፋጣኝና የማያወላውል አብዮታዊ እርምጃ እንደሚወሰድ የማያበስር ሲሆን ሐቀኛ ተራማጆችም የሚጠይቁት ይህንኑ ነው ። ደርግ ለቢሮክራሲው እንዲሳሳ የሚማጠኑት ኃይሎች ለማስረሳት የሚፈልጉት ነገር ፣ ቢሮክራሲው ጊዜውና ሁኔታ ከፈቀደለት ደርግንና የኢትዮጵያን አብዮት እንደ "ብርጭቆ" ከመከስከስ እንደማይመለስ ነው ። በዚሁ አንፃር የቺሊ ታሪክ ዓይነተኛ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል ። እነ አዬንዴ በየዋህነታቸው ቢሮክራሲው ታማኝ ነው ብለው ስለሳሱለት ፣ አድሃሪው ቢሮክራሲ በዚሁ ሁኔታ ተጠቅሞ በቺሊ ሕዝብ ላይ ሊያደርስ የበቃውን እልቂት ሁላችንም የምናውቀው ነው ። የኢትዮጵያ ተራማጆች የሚጠይቁት ቢሮክራሲው እንዳለ ከመቅጽበት ይበተን ሳይሆን ፣ ቢሮክራሲውን ለመደምሰስ በምናደርገው ዘመቻ ባንድ በኩል ቢሮክራቶች ሊኖራቸው በሚችል ኤክስፐርት ዕውቀት እየተጠቀምን ፣ በሌላው በኩል ቁልፍ ቦታዎችን የያዙ አድሀሪያንን እንስተን በተራማጆች መተካትን እናፋጥን ነው ። ማለትም በመጀመሪያ ደረጃ አድሀሪያን ከአመራር ቦታዎች እንዲወገዱ ነው ። የአብዮቱ ጥያቄ ይህ ሆኖ ሳለ ፣ ይህን ጥያቄ የሚፃረሩ ኃይሎች ሀገራችንን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት በቢሮክራቶች አመራር ሥር እንዲውል ይጠይቃሉ ! የሀገራችንን መከላከያ ማደራጀታቸው ቀርቶ (ከጠላት ጋር ስላላቸው የውስጥ ለውስጥ ግንኙነት እናነሳባቸውም) በዚሁ ማጥ ውስጥ እንድንገባ የደረጉን ቢሮክራቶቹ ናቸው እላለሁኝ ። በምሳሌዎች ላስረዳ ። ሱዳንና ግብፅ በአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝም አቀነባባሪነት ካለፈው ዓመት

ጀምሮ በኢትዮጵያ ላይ አድሃሪ ሴራቸውን
ሲሸርቡ የኛ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ክፍሉ
ወዳጆና ያሸማቸው አድሃሪ ዲፕሎማቶች
ምን አደረጉ ? አስፈላጊውን ዲፕሎማቲክ
እንቅስቃሴ አካሄዱ ወይ? ወታደራዊ ዝግጅ
ታችንን እንድናጠነክር አሳሰቡ ወይ ? አድ
ሃሪው የማስታወቂያ ሚኒስቴር ቋሚ ተጠ
ሪያችን የነበረው ተስፋዬ ታደሰ ለሰፊው የ
ዓለም ሕዝብ በኢትዮጵያ ላይ የተጠነሰሰ
ውን ሴራ አጋለጠ ወይ? በቅስቀሳ ደረጃ ዓ
ለም አቀፍ ወዳጆችን አፈራልን ወይ? ሌሎ
ችም ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻል ነበር ።
በእኔ ግምት አድሃሪ ቢሮክራቶች ቁልፍ
የአመራር ቦታ ባይዙ ኖሮ አሁን ለገጠመን
ችግር በበለጠ በተዘጋጀን ነበር ። የሀገራ
ችንን መከላከያ ጥረት በቢሮክራሲው እጅ
እንዲገባ እንጂ ፣ በተራማጆች አመራር
ሥር እንዳይውል የሚቀረበው ሌላ ምክን
ያት <u>አንድ ወይም ሁለት ተራማጅ ድርጅ
ቶች ሊጠናከሩበት ይችላሉ</u> የሚለው ነው ።
ይኸ <u>መቼም አብዮታዊ አቋም ሊሆን አይ
ችልም</u> ። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ብሔራዊና
አብዮታዊ ጥቅም ከማናቸውም ተራማጅ
ድርጅት ጥቅም ይበልጣል ። ማሰብና ማድ
ረግ ያለብን ሁል ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝ
ቦች ጥቅም በተቀዳሚ ደረጃ በመመልከት
ነው ። የኢትዮጵያን አብዮትና ሕዝቦችን
ጥቅም በራሳቼን ጠባብ ጥቅም የሌካነውና
የመጠነው እንደሆን ፣ በአብዮታችን ላይ
የምናደርሰው ጉዳት በቀላሉ ሊገመት የማ
ይችል መሆኑን መዘንጋት የለብንም ።

2\. <u>በውጭ ኃይል መተማመን</u> ፣ በሰፊው ሕዝ
ብ አብዮታዊነትና ሀገር ወዳድነት ፣ እንዲ
ሁም በሀገር የመከላከል ችሎታው ላይ እም
ነት አጥተን ፣ ወዳጆቻችን በሚለግሱን
ዕርዳታ ላይ ብቻ <u>ተስፋችንን መጣል ሌላ
ልንፈጽመው</u> የምንችለው ስህተት ነው ።
አብዮት የአንድ ሕዝብ ነፃ ታሪካዊ ድር
ጊት ነው ። አብዮቱን ከውስጥና ከውጭ
የሚፈታተኑትን ጠላቶች መቋቋም የታ
ሪክ አድራጊው የሰፊው ሕዝብ ፈንታ
ነው ። እጁን በማጠፍ ወደኋላ ተቀምጦ
በምትኩ ሌሎችን ማዋጋት አይችልም ።
አለበለዚያማ የሚደረገው አብዮት ሀቀኛ
አይደለም ፣ በሕዝብ የተደገፈ አይደለም
ማለት ነው ። የዚህም ዓይነት አብዮት ሊኖ
ር እንደማይችል ግልጽ ነው ፣ ስለዚህም
በማናካሂደው የሀገር መከላከያ ሕዝባዊ አ
አብዮታዊ ጦርነት በተቀዳሚው ደረጃ በ
ሕዝባችን አብዮታዊ ኃይል እምነት በመ
ጣል ፣ ከውጭ የምናገኘውን ዕርዳታ እንደ
ደጋፊ ኃይል ብቻ መመልከት ይኖርብናል፤

3\. <u>ጠላትን መናቅ</u> ፣ ጠላትን መናቅ አንድ ልን
ፈጽመው የምንችለው ስህተት ፣ በራሳችን
ወታደራዊ ችሎታ ከመጠን በላይ በመተ
ማመን ፣ የከበቡንን ጠላቶች ያለ አግባብ
መናቅ ነው ። እርግጥ የኢምፔሪያሊስት
ቡችሎች በመሆናቸውና በመጨረሻ ደረ
ጃም እኛ እንደምናሸንፋቸው ስለምናውቅ
ልንንቃቸው እንችል ይሆናል ። ነገር ግን
በተወሰነ ወቅት ሊያስልፉ የሚችሉትን
ሠራዊት ፈጽመን መናቅ አይገባንም ።
እንደሁኔታውና እንዳመጣጣቸው ያላቸው
ን ወታደራዊ ችሎታ በትክክልና በሚገባ
ማመዛዘን መቻል አለብን ። የውትድርና
ታሪክ እንደሚያስተምረንም ጠላትን
መናቅ ብዙውን ጊዜ መሸነፍን መጋበዝ
ነው ፣ የተናቀውም ጠላት ያልጠበቅነውን
እርምጃ ሲወስድብን ብርክን ያስከትል
ብናል ።

4 <u>ከመደበኛ ሠራዊታችን በስተቀር የተቀሩ
ትን የታጠቁትን የሕዝብ ክፍሎች ለምሳሌ
እንደ ሕዝባዊውን ሠራዊት መናቅ ፣ ችላ
ማለት</u> ፣ ይህ ስህተተኛ አስተሳሰብ የሚገለ
ጠው ሕዝባዊውን ሠራዊት በሚገባ ባለ
ማሠልጠን ፣ ባለማደራጀትና ባለማስ
ታጠቅ ነው ። ግፋ ቢል ሕዝባዊው ሠ
ራዊት መደበኛው ሠራዊትን እያስከ
ተለ ፣ ለርሱም ረዳት በመሆን ሊያገለግል
እንደሚችል ይቆጠራል ። ይህ በአብዮቱ
ም ሆነ በውትድርና አንፃር ፈጽሞ የተሳሳ
ተ ታክቲክ ነው ። እንደኛ ሠራዊትሆነ



ጠብቅ የተለኘውን ተቀዳሚ ወታደራዊ
ዊ መርሆ ይቃረናል ። ማለትም በዚሁ
አኳኋን በከንቱ የብዙ ሰው ሕይወትና መ
ሣሪያ ይወድማል ። ሁለተኛ ሕዝባዊ ሠራ
ዊት ሊያበረክተው በሚችለው አስተዋ
ፅዖ መጠቀም አለመቻል ነው ። ሦስተኛ ፣
ይህ ዓይነት ስህተት ከሰፊው ከተፈጸመ
የሚታገልልን ሕዝባዊ ሠራዊት ማጣታ
ችን የማይቀር ነው ።

እነዚህ ከላይ የዘረዘርኳቸውንና እነርሱን
የመሳሰሉ ስህተቶች ከመፈጸም ተቆጥበን (የነ
ዚሁ ስህተቶች ዋና ምንጭ በቀላሉ ለማየት እን
ደሚቻለው ስሜታዊነት (subjectivism) ነው፤
በቅንነትና በሙሉ ልባችን ሕዝባችንንና ሀገራ
ችንን ለማገልገል ቆርጠን ከተነሣን ማናቸው
ንም ወራሪ በማያወላውል አኳኋን እናሸንፋ
ለን ።

ሕዝባዊ ጦርነት ያሸንፋል !